# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ

81ኛ ዓመት ቁጥር 361 ጳጉሜን 1 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## የአሸባሪው ትህነግ ሶስተኛ ዙር ጦርነት የተሰጠውን ተደጋጋሚ የሰላም እድል ያመከነበት ነው

-አቶ ብናልፍ አንዷለም የሠላም ሚኒስትር

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የአሸባሪው ትህነግ ሶስተኛ ዙር ጦርነት የተሰጠውን ተደጋጋሚ የሰላም እድል ያመከነበት መሆኑን የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዷለም ገለጹ።

የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደገለጹት፤ መንግሥት ለሠላም ካለው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ ሕወሓት ወደጦርነት እንዳይገባ እና ችግሮችም በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ በርካታ ሙከራዎችን አድርጓል።

አቶ ብናልፍ እንደተናገሩት፤ የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች ስለሠላም ቡድኑ ያለበት ሄደው የሠላም ጥሪ እንዲያቀርቡ ተደርጓል። ከዚህም በተጨማሪ በርካታ የሰላም ጥሪዎች ቀርበውለታል። ቡድኑ ይህን አልቀበል ሲል ደግሞ ከመንግሥትና ከሌሎች ኃይሎች ገለልተኛ የሆነ የምክክር ኮሚሽን እንዲቋቋም ተደርጎ ችግሩን በሰላም ለመፍታት ብዙ ርቀት ተሂዷል።

ከዚህም ባለፈ ለሰላም ተጨማሪ እድል ለመስጠት እና የትግራይ ህዝብ የግብርና

የአሸባሪው ትህነግ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ትህነግ በተፈናቃይ ስም ሰርጎገቦችን ወደ አማራ ክልል ለማስገባት መወሰኑን ሾልኮ የወጣው ሚስጥራዊ ሰነድ አጋለጠ

- በወልዲያ ከተማ የትህነግ ታጣቂዎችን ጨምሮ 71 ሰርጎገቦች ተያዙ

**በጌትነት ተስፋማርያም**

ወልዲያ፡- ሰሞኑን ሾልኮ የወጣው የትህነግ ሚስጢራዊ ሰነድ "ወደ አማራ ክልል በተፈናቃይ ስም ኃይል ማስገባት አለብን" የሚል ውሳኔ ማሳለፉን አጋለጠ። በወልዲያ ከተማ በተደረገ ቁጥጥርና ፍተሻ የትህነግ ታጣቂዎችን ጨምሮ 71 ሰርጎ ገቦች መያዛቸውን የከተማ አስተዳደሩ አስታወቀ።

የወልዲያ ከተማ ተቀዳሚ ምክትል ከንቲባ ዶክተር ዳዊት መለሰ በከተማዋ ለሚገኙት የኢፕድ ዘጋቢዎች እንዳስታወቁት፤ በከተማዋ በተዘጋጁ እያንዳንዱ ኬላዎችና የፍተሻ ጣቢያዎች ላይ ጠንካራ የጸጥታና ቁጥጥር ስራ እየተከናወነ ይገኛል።

ያለፍቃድ መሳሪያ የያዙ፤ የተለያየ ንብረት ያሸሹና

ትህነግ በተፈናቃይ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ






አርሾ
ሜዲካል ላቦራቶሪ ኃ.የተ.የግ.ማ
ARSHO MEDICAL LABORATORIES P.L.C
በትውልድ የታመነ!
አድራሻ - አራት ኪሎ፣
ከአራዳ ክፍለ ከተማ ሕንፃ ጀርባ፣
የ24 ሰዓት አገልግሎት
612
0114-16-70-89
0911-10-18-18


## በክረምቱ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከ8 ሺህ በላይ ቤቶች እየተገነቡ ነው

- በጳጉሜን ወር ለ130 ሺህ ዜጎች ማዕድ የማጋራት ሥራ ይከናወናል

ገጽ 4

## የዓባይ ግድብ ቀጣናዊ ትሥሥርን ያጠናክራል

ገጽ 4




ገጽ 3

## "ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ የሕወሓትን የወረራ ድርጊት በይፋ አለማውገዙ ጦርነቱን ከመደገፍ እኩል ነው"

- አቶ ሐሳቡ ተስፋው በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የሥነ ዜጋ ሥነምግባር ትምህርት ክፍል መምህር



ዜና


ፎቶ ሐዱሽ አብርሃ
አቶ ቢተው ሸባባው

# የአረንጓዴ አሻራው ለግድቦች ህልውና ዋስትና ነው

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተከናወነ ያለው የአረንጓዴ ልማት አሻራ አስተማማኝ ዝናብ እንዲኖር እና ወንዞች ተፈጥሮአዊ ፍሰታቸው ተጠብቆ እንዲቆዩ ከማድረግም ባሻገር ግድቦች በደለል እንዳይሞሉ ዋስትና እንደሚሆን የኢትዮጵያ ደን ልማት አስታወቀ፡፡

በኢትዮጵያ ደን ልማት የደን ልማት ዳይሬክተሩ አቶ ቢተው ሸባባው በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት ተቋሙ እንደ ሀገር የደን ልማቱን በማስተባበር በደን ጥበቃና አጠቃቀም ዙርያ ያሉትን እንቅስቃሴዎች የሚያስተባብር ተቋም ከመሆኑም ባሻገር ኢትዮጵያ በአህጉርና ዓለም አቀፍ ደረጃ የገባችውን ቃል እንድትፈፅም ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡

የሚተከሉ ችግኞችና የደን ልማቶች ደለልን በመከላከልና ተራሮችን የውሃ ማማ በማድረግ ፍሰቱ የተስተካከለ ውሃ እንዲኖር ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ቢተው፤ የተፈጥሮ ደኖችንና አሁን እየተተከሉ ያሉ ችግኞችን መጠበቅ ተገቢ ተግባር መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

የዚህን ዓመት ጨምሮ ላለፉት አራት ዓመታት በርካታ ቁጥር ያላቸው ችግኞች በመተከላቸው ማህበረሰቡ የኔነት ስሜት እንዲያዳብርና ግንዛቤው እየጎለበተ በመምጣቱ ከዚህ በፊት ከነበሩት የመፅደቅ ምጣኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፣ በኢትዮጵያ ወደ 54 ሚሊዮን ሄክታር የተራቆተ መሬት እንዳለ የሚያመላክቱ ጥናቶች የሚያሳዩ ሲሆን በአረንጓዴ ልማት አሻራዎች አማካኝነት እስካሁን በተተከሉ ችግኞች በርካታ ተራቁተው የነበሩ መሬቶች እንዲያገግሙ ሆነዋል፡፡

ተራቁተው የነበሩ መሬቶች በማገገማቸውና በመመለሳቸው የአፈር ክለትን በመቀነስና የውሃ ስርገት እንዲኖር በማድረግ የአፈር ለምነት እንዲጨምር ያደርጋሉ ያሉት አቶ ቢተው፣ ደለሎችን በመቀነስ ረገድ በተለይም እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ያሉ ግዙፍ ግድቦች በደለል እንዳይሞሉ ያደርጋሉ ብለዋል፡፡

በተለይም ተራራዎች በሚራቆቱበት ወቅት ከተራራዎች ላይ የሚነሳው ደለል ወደ ታችኛው ተፋሰስ አካባቢ በመሄድ ግድቡን የሚሞላ በመሆኑ ግድቡ የሚሰጠውን የአገልግሎት ጊዜ በማሳጠር ለኪሳራ ይዳርጋል ብለዋል፡፡

በመሆኑም በላይኛው ተፋሰስ ላይ የሚከናወነው የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ለሆኑት ግብፅና ሱዳን ሀገራት ላይ ለሚገኙ ግድቦችም ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ተናግረዋል፡፡

በመሆኑም በየጊዜው የምንተክላቸውን ችግኞች በተተከሉ ሁለት ሳምንታት ውስጥ በመጎብኘት የሞቱ ችግኞች ካሉ በመተካት፣ አረሞችን በተገቢው በማረም፣ ከልቅ ግጦሽ በመጠበቅና እርጥበት ባለበት ወቅት ኩትኳቶ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አብራርተዋል፡፡

በተለይም በተራቆቱ አካባቢዎች የሚተከሉ ችግኞች ተጨማሪ ግብአት በማከል እንዲያድጉ በማድረግ አካባቢው እንዲያገግም ማድረግ ተገቢ ነው ያሉት የደን ልማት ዳይሬክተሩ፣ በግለሰብ፣ በተቋም እንዲሁም በቡድን ደረጃ ለተተከሉ ችግኞች ዓመቱን ሙሉ ክብካቤ መደረግ አለበት በማለት ምክረ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ደን ልማት የተተከሉ ችግኞች እንዳይጠፉና ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ እንዲያገኙ ከተለያዩ አጋር ተቋማት ጋር በመሆን በየወቅቱ ግንዛቤ የመስጠት፣ ከፌዴራል እስከ ቀበሌ ድረስ ባሉ ሙያተኞች አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ በመስጠት እንዲሁም ከተለያዩ መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ የሚታይ ተግባር እያከናወነ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

# “ህወሓት የትግራይን ወጣት ወደ ጦርነት እየማገደ ክልሉን ትውልድ አልባ የማድረግ ዓላማውን ገፍቶበታል”

- ምርኮኞች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



**አዲስ አበባ**፡- አሸባሪው ህወሓት በሃሰተኛ ትርክት የትግራይን ወጣት ራሱ ወደ ለኮሰው ጦርነት እየማገደ ክልሉን ትውልድ አልባ የማድረግ እኩይ አላማውን ገፍቶበታል ሲሉ ምርኮኞች ገለጹ፡፡ አሸባሪው ህወሓት የሰላም አማራጭን ረግጦ ጦርነት መክፈቱ በትግራይ ህዝብ ጫንቃ ላይ ቆሞ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም መሆኑንም መስክረዋል፡፡

በተለያዩ ግንባሮች እጃቸውን ለጀግና መከላከያ ሰራዊት የሰጡ ምርኮኞቹ እንደተናገሩት፤አሸባሪው ሕወሓት የትግራይን ህጻናት ሳይቀር ወደ ጦር ግንባር እየማገደ ይገኛል፡፡ ይህም ተግባሩ የሽብር ቡድኑን የባንዳነት ትክክለኛ ባህሪ በተጨባጭ እያረጋገጠ ነው።

ምርኮኞቹ አሸባሪው የህወሓት ቡድን በትግራይ ህዝብና ህፃናት ላይ እየፈፀመ ያለውን ስቃይና እንግልት በመቃወም በፕሮፖጋንዳ ተታለው ከገቡበት ጦርነት በመውጣት ለጀግናው የሀገር መከላከያ ሰራዊት እጃቸውን መስጠታቸውን ገልፀዋል።

የሰላም አማራጭ በሰፊው ቀርቦለት ጦርነትን መርጦ ህጻናትን ሳይቀር ወደ ጦርነት እየማገደ ያለው የሽብር ቡድኑ ህወሓት የራሱን የስልጣን ላይ ቆይታ ለማራዘም ትግራይ ላይ ምንም አይነት ጥፋት ከመፈጸም ወደኋላ እንደማይመለስ ምርኮኞቹ አረጋግጠዋል።

"የትግራይ ከፍታ የሚረጋገጠው በኢትዮጵያ መቃብር ላይ ነው" በሚል ቀቢፀ ተስፋ በመነሳሳት ኢትዮጵያን ለማፍረስና ህዝቦቿን ለመበተን ዳግም ጦርነት ቢከፍትም ዓላማ ቢስ ለሆነው የሽብር ቡድኑ አላማ መሰለፍ ከንቱ በመሆኑ እጃቸውን ለመስጠት እንዳስገደዳቸው ተናግረዋል።

በቡድኑ የውሸት ወሬና ፕሮፓጋንዳ ተታለው በመሰለፍ ለፈፀሙት ጥፋት በመፀፀት ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ፤ ለመከላከያ ሰራዊቱና ለሌሎች የፀጥታ ኃይል ይቅርታ ጠይቀው ፤የህወሓት የሽብር ቡድንን ከንቱ ራስ ወዳድ አላማ ለማስፈፀም የተሰለፉ የትግራይ ወጣቶችም የሚጓዙበት መንገድ ፈጽሞ እንደማያዋጣ ተረድተው ፈጥነው እንዲነቁ ምርኮኞቹ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

ምርኮኞቹ በመከላከያ ሰራዊትና በሌሎች የፀጥታ ኃይሎቻችን ለተደረገላቸው መልካም አቀባበልና እንክብካቤም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ከጦርነት ኪሳራ እንጂ ትርፍ እንደማይገኝ የገለፁት ምርኮኞቹ፤ አሸባሪ ቡድን ለዳግም እልቂት የከፈተውን ወረራ በማውገዝ ወደ ሰላም እንዲመጣ የትግራይ ህዝብ፤ ወጣቶችና ልዩ ኃይል አባላት ጫና መፍጠር እንደሚገባቸው ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

የትግራይ ህዝብ መሞትና መራብ ለሽብር ቡድኑ የፕሮፖጋንዳ መጠቀሚያ ነው ያሉት ምርኮኞቹ፤ "አሸባሪው ህወሓት በሃሰተኛ ትርክት የትግራይን ወጣት ራሱ ወደለኮሰው ጦርነት እየማገደ ክልሉን ትውልድ አልባ የማድረግ እኩይ አላማውን ገፍቶበታል ብለዋል፡፡

አሸባሪው ህወሓት ከባድ አደንዛዥ እፅ እንዲጠቀሙ በማስገደድ ወደማይወጡት ጦርነት እየማገዳቸው መሆኑን በሰቆጣ ግንባር እጁን የሰጠው ሲሳይ ወልደስላሴ መስክሯል።

በአሸባሪው ህወሓት ታጣቂዎች ከየቤታቸው በግዴታ እንደታፈሱ የሚናገረው ሲሳይ፤ ልጆቻቸውን የደበቁ እና አልሰጥም ያሉ ወላጆች ላይም ግድያን ጨምሮ አሰቃቂ ግፍ እንደሚፈፀም ተናግሯል።

አሸባሪ ቡድኑ ፍፁም ሰብዓዊነት በጎደለው መልኩ ለጦርነት ያሰለፋቸው ህፃናት ከባድ አደንዛዥ እፅ እንዲጠቀሙ በማስገደድ ወደማይወጡት እሳት እየማገዳቸው መሆኑን እጁን ለመከላከያ የሰጠው ሲሳይ ወልደስላሴ ማጋለጡን ኢቢሲና ከሠራዊቱ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# የንፋስ መውጫ ሆስፒታልን ለመደገፍ የመግባቢያ ስምምነት ተደረገ

**በኃይሉ አበራ**

**አዲስ አበባ**፡- ዓለም-አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት እና የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር በጎንደር ንፋስ መውጫ ሆስፒታልን ለመደገፍ እና በረጅም ጊዜ እቅድ አብሮ ለመስራት የመግባቢያ ስምምነት አደረጉ።

በጎንደር ለሚገኘው ንፋስ መውጫ ሆስፒታል የአንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር የህክምና ቁሳቁስ ድጋፍ ለማድረግም በኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር እና በዓለም-አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት ድርጅት መካከል ስምምነት ላይ ተደርሷል።

በኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አለማየሁ መኮንን እና የግሎባል አልያንስ ፎር ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ በትሩ ገብረ እግዚአብሄር መካከል በኢትዮጵያ ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ በተለይም በጤና መስክ የደረሱ ጉዳቶች ለመደገፍ በጋራ ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አለማየሁ መኮንን ዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት ድርጅት ጋር በጋራ ለመስራት ከዚህ በፊት ተደጋጋሚ ውይይቶች መደረጋቸውን አስታውሰዋል።

በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት የወልዲያ ጤና ጣቢያ ድጋፍ ለማድረግ በተደረገ ስምምነትም የህክምና ቁሳቁስ አቅርቦት በማድረግ ጤና ጣቢያው በተሻለ ቁመና ላይ ሆኖ አገልግሎት መስጠት በሚችልበት ደረጃ እንዲደርስ አድርገናል። በሁለትዮሽ ትብብሩ ከወዲሁ ጤና ድርጅቶቹ ሥራ ጀምረው የህክምና ቁሳቁሶችን እና ወሳኝ የጤና ግብዓቶችን በማግኘት ኅብረተሰብን ወደ ማገልገል ሥራ እንዲገቡ ለማድረግ እና በረጅም ጊዜ ዕቅድም አብሮ የመስራት ፍላጎቶችን ጎን ለጎን እያስኬድን ነው ብለዋል።

በዚህ ስምምነትም የንፋስ መውጫ ሆስፒታልን አሁን ከሚገኝበት ቁመና የተሻለ በማድረግ ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት የሚያጠናክር መሆኑን አመላክተዋል። በስምምነቱ መሰረትም የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር በተለይ የህክምና ቁሳቁሶችን ገዝቶ በማቅረብ ለሆስፒታሉ ያደርሳል ብለዋል።

ከሰሜን አሜሪካ የመጡት የዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት ግብረሰናይ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ በትሩ ገብረእግዚአብሄር ድርጅቱ በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ በተፈጠረው ጦርነት ለተፈናቀሉ ዜጎች አስቸኳይ ድጋፍ በማድረግ ረገድ ላለፉት ሁለት ዓመት ተኩል ሲሰራ ቆይቷል ብለዋል።

እ.አ.አ በ2013 ዓ.ም ሳውዲ አረቢያ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ህጋዊ አይደላችሁም በሚል በአንድ ጊዜ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ዘመቻ በተደረገባቸው ጊዜ የተመሰረተው ድርጅት በወቅቱ ኢትዮጵያውያን የተለያዩ እንግልት ሲደርስባቸው በቪድዮ በማየት በመላው ዓለም በሚገኙ የሳውዲ ኤምባሲዎች ላይ በአንድ ቀን በአንድ ጊዜ ሰላማዊ ሰልፍ እንዲደረግ በማድረግ ከፍተኛ ጫና መፍጠር ተችሏል። በሳውዲ አረቢያ መንግሥት ወጪ እና በዓለም አቀፍ የስደተኞች ተቋም አመቻችነትም በሁለት ሳምንት 163 ሺህ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው እንዲመለሱ መደረጉን አስታውሰዋል።


ድርጅቱ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ዲያስፖራውን በማስተባበር በስደት በጦርነት፣ በድርቅ እና በተለያየ መንገድ ጉዳት የደረሰባቸው ወገኖችን እየደገፈ መቆየቱን ገልጸው እስካሁንም ከ250 እስከ 300 ቢሊዮን ብር የሚደርስ እርዳታ ማድረጉን ተናግረዋል።

ጦርነቱ እንደተጀመረ የቆሰሉትን ማከሚያ እና በቶሎ እንዲያገግሙ የሚረዳ ድጋፍ በጎንደር እና በጦርነቱ ቀጠና አቅራቢያ ድጋፍ መደረጉን አስታውሰዋል። የሰብዓዊ መብት ጥሰት ለደረሰባቸው ወገኖች የሚደረገው ድጋፍ ኢትዮጵያውያን ወገን አለን ብለው በአገራቸው እንዲኮሩ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

በቀጣይ የጤና ፕሮጀክትም ደላንታ ሆስፒታል ለመደገፍ የሚውል ስድስት ሚሊዮን ብር በላስቬጋስ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ማህበር ለዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት ድርጅት ገቢ ያደረጉ እና በቅርብ ጊዜ ሥራ ላይ የሚውል መሆኑንም ጠቁመዋል።

# ትህነግ በአማራ ሕዝብ ላይ የፈፀመውን ግፍ የሚያሳይ የጥናት ውጤት በመጽሐፍ መልክ ተዘጋጀ

**ሞገስ ተስፋ**




ጐንደር:- የጎንደር ዩኒቨርሲቲ አሸባሪው ትህነግ ላልፉት አራት አስርት ዓመታት በአማራ ሕዝብ ላይ የፈፀመውን ዘር ተኮር ፍጅት፣ የቋንቋ ፣ባህል ማጥፋትና ዘርፈ ብዙ ጥቃቶችን የሚያስረዳ “ወረራና መዋቅራዊ የዘር ማጥፋት በወልቃይት ጠገዴ ጠለምት” የተሰኘ የምርምር ውጤት በመጽሐፍ መልክ ታትሞ በዛሬው እለት ለህዝብ ይፋ አድርጓል።

አሸባሪው ህወሓት ወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምትን በሃይል ተቆጣጥሮ በነበረበት ዘመን በህዝቡ ላይ ያደረሳቸው ታሪካዊ፣ ማህበራዊ፣ ሰብአዊና ኢኮኖሚያዊ ግፎችን የጐንደር ዩኒቨርሲቲ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመጽሐፍ መልክ ለህዝብ ይፋ አድርጓል።

በዚሁ ስነስርዓት ላይ የጐንደር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር አስራት አጸደወይን እንደተናገሩት፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዋና አላማ በምርምር እውነትን መፈለግ ነው። ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ህዝብ ላይ አሰቃቂ የሆነ መዋቅራዊ የዘር ማጥፋት ማካሄዱን ዩኒቨርሲቲው 21 አባላት ያሉት የጥናት ቡድን አቋቁሞ ለ18 ወራት ሳይንሳዊ ጥናት አድርጓል።

እንደ ዶክተር አስራት ገለጻ፣ የጥናቱ አላማ ጥላቻን ለማስፋት ሳይሆን እልባት በመስጠት ሰላምን ለማስፈን ነው። ችግሮችን ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት በቂ እውቀት ሊኖር ይገባል። የምርምር ውጤት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት የተፈፀመውን ዘግናኝ ግፍ ለዓለም ማህበረሰብ የሚያሳይ ነው።

ዶክተር አስራት መጽሐፉ “ወረራና መዋቅራዊ የዘር ማጥፋት በወልቃይት ጠገዴ ጠለምት” የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን በሰባት ምእራፎች 387 ገጾች በአምስት ሺ ኮፒዎች ታትሟል። በዘር ፍጅት፣ ፆታዊ ጥቃት፣ የታሪክና ማንነት ወረራና ኢኮኖሚያዊ ምዝበራ፣ በጤና እና ትምህርት ላይ የተፈፀመ ግፍና ሌሎችም ዘርፎችም ላይ በጥልቀት መረጃዎች የተሰባሰቡበት ነው ብለዋል።

መጽሐፉ ዘግናኝና አሰዋቂ የጅምላ ግድያ የተፈጸሙበትን ግፍ ቁልጭ አድርጐ የሚያሳይ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ጥፋተኛ ጥፋቱን አውቆ በይቅርታ የሚመለሰው እውነት ሲወጣ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ጥናቱን ማካሄዱን ዶክተር አስራት አብራርተዋል።

የአማራ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ጌታቸው ጀምበር በመጽሐፉ ምረቃ ላይ ባደረጉት ንግግር የወልቃይት ጠገዴ ጠለምት አካባቢ በአሸባሪው ቡድን የተፈጸመው ግፍ ቆሞ የሚመሰክር ነው። ይህን ግፍ የጐንደር ዩኒቨርሲቲ በጥናት በተረጋገጥ እውነትን ለህዝብ ይፋ ማድረጉ ምስጋና የሚገባው ነው ብለዋል።

አሸባሪው ትህነግ በስልጣንና በሽፍትና ዘመኑ በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት አካባቢ ወጣቶች ያለመካሪ ፣ አባቶች ያለጧሪ፤ ህጻናት ያላሳዳጊ እንዲቀሩ ማድረጉን ጠቁመዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ ማህበራዊ ዘርፍ አማካሪ ሙአዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በበኩላቸው ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፣ የጐንደር ዩኒቨርሲቲ በወልቃይት፣ ህወሓት ጠገዴና ጠለምት ያደረሰውን ግፍ በጥናት ለይቶ አቅርቧል። ዩኒቨርሲቲዎች ከመሽኮርመም ወጥተው እውነትን በጥናት ማቅረብ አለባቸው ብለዋል።

በአካባቢው የተፈጸሙ ግፎችን በመዘከር ለመካስ ትውልዱን ወደፊት እንዲፈነጠር መስራት ያስፈልጋል ያሉት አማካሪው፣ በአይሁድ ላይ የተፈጸመውን ጭፍጨፋ አልተፈጸመም ማለት እንደወንጀል ይቆጠራል። ልክ እንደዚህ ሁሉ በኢትዮጵያም እንደ ወልቃይት ያሉ አካባቢዎች ከግፍ ወጥተው እንደማንኛውም አካባቢ መኖር አለባቸው ብለዋል።

ስለሆነም ትውልዱ ግፉን በመዘከር ወደፊት በልማት መስፈንጠርና አካባቢንና አገርን መለወጥ ያስፈልጋል። አካባቢ ከደረሰበት ጉዳት እንዲያገግም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ውሳኔ ያስፈልጋል ብለዋል።ጥናታዊ መጽሐፉ ለሌሎች ጥናቶች መነሻ እንዲሆን በአግባቡ የተደራጀ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

# ኢትዮጵያ ፈተናዎችን ተቋቁማ በተለያዩ መስኮች ስኬት አስመዘገባለች

ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ:- ኢትዮጵያ በ2014 በጀት ዓመት ያጋጠሟትን ፈተናዎች ተቋቁማ በኢኮኖሚው፤ በፖለቲካው እና በሰላምና ደህንነት መስኮች ስኬታማ ሥራዎችን ማከናወኗ ተገለጸ። አዲሱ ዓመት ለኢትዮጵያ ብሩህ እንደሚሆን ተገልጿል።

የፕላንና ልማት ሚኒስትሯ ዶክተር ፍጹም አሰፋ ‘ፈተና፣ ድል፣ ተስፋ’ በሚል ርዕስ የ2014 በጀት ዓመትን ዐበይት የመንግሥት የሥራ ክዋኔዎች የሚዳስስ የአዲስ ወግ የውይይት መርሀ ግብር ትናንት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ሲካሄድ እንደገለጹት፤የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሰሜኑን ጦርነት ጨምሮ ብዙ የውጭና የአገር ውስጥ ፈተናዎች ቢያጋጥሙትም እነዚህን ተቋቁሞ ዕድገት ማስመዝገብ ችሏል።ዕድገቱም የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ በውጭ ምንዛሬ ግኘት፣ምርትና ምታማነትነት በማሳደግ እና የውጭ ኢንቨስትመንት በመጨመር ረገድ ተጨባጭ ለውጥ የታየበት ነው።

የኢኮኖሚ ዕድገቱ አንዱ መለኪያ ዜጎችን የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ማድረግ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ፍጹም፤ በበጀት ዓመቱ ለሁለት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ዜጎች አዳዲስ ቋሚ የሥራ ዕድል መፈጠራቸውንና እነዚህ ዜጎች የሥራ ዕድል ተጠቃሚ መሆናቸውና ገቢ ማግኘታቸው አንዱ ስኬት መሆኑን ተናግረዋል።

ሌላው የኢኮኖሚ ዕድገቱ ማሳያ ከሆኑት አንዱ የውጭ ምንዛሪ ግኘት መሆኑን ጠቅሰው፤ ባለፈው በጀት ዓመት ከሸቀጥ ንግድ ፣ከአገልግሎት፤በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለዘመዶቻቸው ከሚልኩት ገንዘብና ከውጭ ኢንቨስትመንት 22 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ የውጭ ምንዛሪ መገኘቱን አብራርተዋል።

በ2014 በጀት ዓመት ዲሞክራሲን ለማጎልበት፣ህብረ ብሄራዊ አንድነትን ለማጠናከር፣ አካታችነትንና የጋራ መግባባትን ለመፍጠር የተሰሩ ሥራዎች ውጤታማ ናቸው ያሉት የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ፣ ይህም በጋራ የሀገርን ሀብት ለማልማት ያስችላል። የተለያየ አመለካከት ሲኖር የሀሳብ ጥራትና የጋራ መግባባት ለማምጣት ያስችላል። ዲሞክራሲና አካታችነት የሚያስፈልገው ለዚሁ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

መንግሥት ህዝብ ያነሳቸውን ጥያቄዎች በመመለስ፣ አንድነትን በማጠናከርና ለተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ስልጣንን በማጋራት ረገድ ውጤታማ ሥራዎች መሰራታቸውን አመልክተው፤ እነዚህን ይበልጥ በማጎልበት የኢትዮጵያን ብሩህ ተስፋ ማረጋገጥ ይገባል ብለዋል።

ጠንካራ አገርና መንግሥት ለመመስረት ጠንካራ ፓርቲ መገንባት ያስፈልጋል ያሉት አቶ አደም፤ የብልጽግና ፓርቲም አመራሩንና ተተኪ ወጣቶችን ለመገንባት እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

የህዝብ ጥያቄዎችን በተገቢው መልኩ ለመመለስ መንግሥት አመራሮቹ ተጠያቂ የሚሆኑበትን አሰራር መዘርጋቱን ገልጸው፤ ይህ ጥረት ስኬታማ እንዲሆን በሚደረገው ጥረት ህዝቡ የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን በጸጥታ ተቋማት የተሠሩ የለውጥ ሥራዎች የሀገራችንን ሰላም ለማስከበርና ሉዓላዊነቷን ለማስጠበቅ፣ የዜጎችን ደህንነት ለማስጠበቅ በሚያስችል አቋም ላይ ይገኛሉ ብለዋል። ጀግናው የአገር መከላከያ በፈተናዎችም ውስጥ ሆኖ ራሱን አደራጅቶ የኢትዮጵያን ህልውና ማስጠበቁ ስኬት ነው ብለዋል።

በአዲስ ወግ የተሳተፉ ታዳሚዎችም መንግሥት በአንድ እጁ ልማት በሌላ እጁ ደግሞ ጠመንጃ ይዞ ያመጣቸው ስኬቶች የሚደነቁ መሆኑን ገልጸው፤ አሁንም ሰላምና ጸጥታ በማረጋገጥ፣ ህዝቡን በማሳተፍና ፈታናዎቹን በግልጽ ከማስረዳት፤የዋጋ ግሽበትን ከመቆጣጠርና አንድነትን ከማጠናከር አኳያ ብዙ ሥራዎች የሚጠብቁት መሆኑን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

# “ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ የሕወሓትን የወረራ ድርጊት በይፋ አለማውገዙ ጦርነቱን ከመደገፍ እኩል ነው”

- አቶ ሐሳቡ ተስፋው በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የሥነ ዜጋ ሥነምግባር ትምህርት ክፍል መምህር

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**



አዲስ አበባ:- ዓለም አቀፍ ተቋማትም ሆኑ ሀገራት ሕወሓት በግልጽ ጦርነት አውጆ ይበልጥ እያሰፋ ባለበት ሁኔታ ቡድኑን ለማውገዝ አለመፈለጋቸው በእጅ አዙር አበጀህ የሚል መልዕክት እንደማስተላለፍ ይቆጠራል ሲሉ በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የሥነ ዜጋ ሥነምግባር ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት አቶ ሐሳቡ ተስፋው ገለጹ።

ቡድኑ ለሚፈጽመው ዘረፋ፣ በትግራይ ሕዝብ ላይ ለሚያደርሰው ወንጀል እና ሰብዓዊ ቀውስ በቀላል መግለጫ ከማለፍ የዘለለ ተጠያቂ እንዲሆን ፍላጎት የሌላቸው እንደሆነም ተናግረዋል።

አቶ ሐሳቡ ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቃምልልስ እንደተናገሩት፤ አሸባሪው ሕወሓት እያደረሰ ለሚገኘው ዘግናኝ ግፍ፣ ዘረፋ እና በትግራይ ሕዝብ ላይ ለሚፈጽመው ሰብዓዊ ቀውስ ተጠያቂ እንዲሆን ከመፈለግ ይልቅ “ሁለቱ ሃይሎች” የቡድኑን ጥፋት ለማድበስበስ ሲሄዱ ይስተዋላል። ከዚህም አልፎ መንግሥትን ተጠያቂ የማድረግ ፍላጎት በስፋት ይስተዋላል።

ሕወሓት በትግራይ በሕዝብ ላይ ለሚያደርሰው ማንኛውም ሰብዓዊ ቀውስ ወያኔን ተጠያቂ አለማድረጋቸው አግባብ አለመሆኑን የጠቆሙት አቶ ሐሳቡ፤ የኢትዮጵያ መንግሥትንና ሕወሓትን አቻ አካላት አድርገው ድርድር አድርጉ እያሉ ማድረግ ተገቢ አለመሆኑን ጠቁመዋል።

እስከዛሬም ወያኔ ዘረፋ ሲፈጽም መቆየቱን በውል የሚረዱ ሲሆን በአሁኑ ወቅትም ለሰብዓዊ እርዳታ ለሚያመላልሱ ተሽከርካሪዎች የሚውል ከግማሽ ሚሊዮን ሊትር በላይ ነዳጅ ከመቐለ ከተማ መስረቁ በቀላል መግለጫ ብቻ አልፈውታል፤ ይህም ሚዛናዊነቱን ያልጠበቀ እና ጫናውን መንግሥት ላይ ለማድረግ የተወጠነ ነው ሲሉም አስረድተዋል።

ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ላይ ሲደረግ የነበረውን ጫና የመቀጠል አዝማሚያ በዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ዘንድ መኖሩን ያመለከቱት ምሁሩ፤ ይህንንም የሚደረገው ዓለም እውነት ወይም ውሸት ነው ከሚለው ይልቅ በትርክት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ነው ብለዋል።

ሕወሓት በሥልጣን ዘመኑ በርካታ የሐሰት ትርክቶችን በመፈብረክ በዲፕሎማሲ ሥራ ብዙ ርቀት ሄዷል፤ አሁን ባለው ሂደትም ሕወሓት በግልጽ ጦርነት አውጆ እያለ የማድበስበስ ሁኔታ ይታያል፤ ቀደም ሲል የነበረው አካሄድም ሕወሓት የሀገር መከላከያን በተኛበት መውጋቱን ሳይሆን ሕወሓት በፌዴራል መንግሥት ተወጋ የሚል ትርክት ነው፤ ይህ የትርክት መዛባት ሆን ተብሎ የሚፈበረክ ነው ሲሉ አስረድተዋል። በዚህም የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ከሕወሓት በስተጀርባ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዳላቸው ያሳያል ሲሉ ተናግረዋል።

ከወያኔ ጋር ለሚኖር የፖለቲካ ልዩነት ብቸኛው መፍትሄ እብሪቱን ማስተንፈስ እና ልኩን እንዲያውቅ ማድረግ መሆኑን የገለጹት አቶ ሐሳቡ፤ በዚህ ልክ እንዲኖር ካልተደረገ በቀጣይም በእብሪት ለመኖር የሚውተረተር ስብስብ ነው ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓትን በጦርነትም ሙሉ ለሙሉ ማሸነፍና ህልውናው እንዲያከትም ካልተደረገም የኢትዮጵያ አስቸጋሪ ፈተና ሆኖ መቀጠሉ አይቀሬ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ አቶ ሐሳቡ ገለጻ፤ በታሪክ ውስጥ አሸባሪውን ሕወሓት የመሰሉ ጽንፈኛ ብሄርተኝነት በጃፓን በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ፤ በጀርመን እና ጣሊያን የነበረው ጽንፈኛ ብሄርተኝነትም ዓለም ለከፋ ሰቆቃ እና ጦርነት ዳርገዋል። ናዚን የመሰሉ ጽንፈኛ ፓርቲዎች ከተሸነፉ በኋላ በመጨረሻ ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ሲወገዱ እንዲሁም ሕጋዊ እውቅና ከተነፈጋቸው በኋላ ዓለም ሠላም ሰፍኖባታል።

ጀርመንም ከዚያን ጊዜ ወዲህ ሠላም ናፋቂ ሀገር ሆናለች። በጃፓንም የሥነ ልቦና ለውጥ ከመጣ በኋላ ሁኔታዎች ተስተካክለዋል። አሁን ባለው ሁኔታ አሸባሪው ሕወሓት የሰለጠነ ፖለቲካ መምራት ስለማይችል ጽንፈኛውን ሕወሓት ሁለመናውን ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት የኢትዮጵያን ሠላምና መረጋጋት መስፈን አለበት ብለዋል።

እንደ አቶ ሐሳቡ ገለፃ፤ የሕወሓትን አካሄድ በወታደራዊ ኃይል ከመደምሰስ ጎን ለጎን በከፍተኛ ደረጃ የዲፕሎማሲ ሥራ ማከናወንና ማጋለጥ ይገባል። ለዚህም ደግሞ ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ሦስተኛ የዲፕሎማቶች መቀመጫ በመሆኗ ይህንን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም እውነታውን የዓለም ማሕበረሰብ እዲረዳ ማድረግ ተገቢ ነው። በዲፕሎማሲው ረገድም አሁንም እየተከናወነ የሚገኘውን ስራ አጠናክሮ መቀጠል ይገባል።

# የዓባይ ግድብ ቀጣናዊ ትሥሥርን ያጠናክራል

**በጸጋዬ ጥላሁን**

አዲስ አበባ :- የዓባይ ግድብ በአገራት መካከል የኃይል አቅርቦት ግዢ ስምምነትና ትብብርን በመፍጠር ቀጣናዊ ትስስርን እንደሚያጠናክር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ገለፁ።

ትናንት በአባይ ወንዝ ፍትሀዊና ምክንያታዊ አጠቃቀም ላይ ያተኮረ የተፈሰስ አገራት የመጀመሪያው የትብብር ጉባኤ በአዲስ አበባ መካሄድ ጀምሯል።

በጉባኤው መክፈቻ ላይ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እንዳሉት፤ የህዳሴ ግድብ በአገራት መካከል የኃይል አቅርቦት ግዢ ስምምነትና ትብብርን በመፍጠር ቀጣናዊ ትስስርን ያጠናክራል። የተፋሰሱ አባል አገራትም ፍትሀዊና ምክንያታዊ የውሃ አጠቃቀም ትብብራቸውን እንዲያጠናክሩም ጠይቀዋል።

የህዳሴ ግድብ በታችኞቹ አገራት ላይ ምንም አይነት ጉዳት ሳያደርስ በፍትሃዊነትና በምክንያታዊነት የኤሌክትሪክ ኃይል እያመነጨ ነው ያሉት አቶ ደመቀ፤ የግድቡ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት መጀመሩ ጠቀሜታው ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለቀጣናውም ጭምር ነው ብለዋል።

ሶስቱም የውሃ ሙሌቶች በፍትሀዊነትና በምክንያታዊነት መርህ ላይ ተመስርቶ መከናወኑን ያወሱት ሚኒስትሩ፤ ይህም በአገራት መካከል የጋራ መግባባት እንዲኖር ያስችላል። በታችኞቹ አገራት ላይም ምንም አይነት ጉዳት እንደማያስከትል ተረጋግጧል ብለዋል።

አክለውም የዓባይ ወንዝ በሰው ሰራሽ፣ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ዕድገት፣ በአየር ንብረት ለውጥና በሌሎች ምክንያቶች ተፅዕኖ እየደረሰበት በመሆኑ አገራት የወንዙን ደህንነት ለማስጠበቅ የራሳቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ አሳስበዋል።

በሌላ በኩል የተፋሰሱ አገራት የትብብር ማዕቀፍ መመስረት የአባል አገራቱ መካከል የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን በመቀነስ ፍትሃዊና ምክንያታዊ አጠቃቀም እየሰፈነ መሆኑን ተናግረዋል።

በፍትሃዊነት ከተጠቀመንበት በቀጣናው በቂ የውሃ ሀብት መኖሩን የጠቆሙት አቶ ደመቀ፤ የዓባይና የሌሎች ድንባር ተሻጋሪ ወንዞች ፍትሃዊ አጠቃቀምን ተቋማዊ ማድረግና ማዕቀፎችን ማጠናከር ያስፈልጋል ሲሉ አሳስበዋል።

የውሃና የኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ በበኩላቸው፤ በተፋሰሱ አገራት ያለውን የውሃ ሀብት በፍትሃዊነትና በምክንያታዊነት ለመጠቀም ቀጣናዊ ትስስርና ትብብርን ማጠናከር አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ለሶስት ቀናት ለሚቆየው የተፋሰሱ አገራት ጉባኤ፤ የተፋሰስ አገራት ተወካዮች፣ ምሁራን፣ ተመራማሪዎች፣ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ተወካዮችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት እየተሳተፉ ነው።

# በክረምቱ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከ8 ሺህ በላይ ቤቶች እየተገነቡ ነው

**- በጳጉሜን ወር ለ130 ሺህ ዜጎች ማዕድ የማጋራት ሥራ ይከናወናል**

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሙሉ ለሙሉና በከፊል እድሳት እንዲሁም በአዲስ መልክ ከ8 ሺህ በላይ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ እየተካሄደ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሕብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ኮሚሽን ገለጸ። የተጠናቀቁት ቤቶች በዛሬው ዕለት ለአቅመ ደካሞች እንደሚተላለፉም ታውቋል።

ከዛሬ ጀምሮ በተከታታይ በሚደረጉ የአምሥት የበጎ ፈቃድ፣ የአምራችነት፣ የሰላም፣ የአገልጋይነት እና የአንድነት ቀናት መርሐ ግብሮችም ከ130 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የማዕድ ማጋራት እንደሚካሄድ አስታውቋል።

ምክትል ኮሚሽነር አቶ ሙሰማ ጀማል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የአቅመ ደካሞች የቤት እድሳት መርሐግብር የዓመቱ ዋና ሥራ ነበረ። በዚህ ዓመት በተለያዩ አካላት ከ8 ሺህ በላይ የሚሆኑ ሕዝብ ተደራሽነት ላይ ያነጣጠሩ ቤቶች ግንባታና እድሳት ተካሂዷል። ከነዚህ ቤቶች ውስጥ የተጠናቀቁት በዛሬው ዕለት ለሕብረተሰቡ የሚተላለፉ ይሆናል።

አቶ ሙሰማ፣ ቤቶቹ በኮሚሽኑ አስተባባሪነት በአዲስ አበባ ከንቲባ፣ በቀዳማዊት እመቤት፣ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት እና በጤና ሚኒስቴር፣ በውሃና መስኖ ሚኒስቴር እንዲሁም በምክትልና ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስተባባሪነት የተገነቡ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ከተገነቡና ከተጠገኑት ከ8 ሺህ በላይ ቤቶች ወደ 774 የሚሆኑት በከንቲባ አዳነች አቤቤ አስተባባሪነት የተገነቡ መሆናቸውንና አዲስ መሆናቸውን አቶ ሙሰማ ገልፀዋል። ቀሪዎቹ 7 ሺህ 300 አካባቢ የሚሆኑ ቤቶችን ደግሞ ከፊሎቹ ፈርሰው የተገነቡ እና ግማሽ ጥገና የተደረገላቸው መሆናቸውን አብራርተዋል።

በቤቶች ጥገና እና ግንባታ ረገድ በተለይ ቂርቆስ፣ ልደታ፣ አዲስ ክፍለ ከተማ እና የካ ክፍለ ከተሞች በተለየ መልኩ ተሠርቶባቸዋል ብለዋል ምክትል ኮሚሽነሩ።

በዛሬው ዕለት ለአቅመ ደካሞች የተሠሩ ቤቶችን ከማስተላለፍ በተጨማሪ ሌሎች መርሐግብሮችም እንደሚካሄዱ አቶ ሙሰማ ተናግረዋል። በመላው የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢዎች የተሠሩ ፕሮጀክቶችን የማስመረቅ እና በዝቅተኛ ገቢ ለሚተዳደሩ ማዕድ ማጋራት መርሐግብርም እንደሚካሄድ አክለው ገልፀዋል።

እንደ አቶ ሙሰማ ገለፃ፤ በዛሬው ዕለት በሚሊኒየም አዳራሽ ለ2 ሺህ 200 ሰዎች ማዕድ ይጋራል። በተጨማሪም በሁሉም ክፍለ ከተሞች ከ1 ሺህ እስከ 1 ሺህ 500 ዜጎች ማዕድ እንዲጋሩ የሚደረግ ሲሆን በወረዳ ደረጃም ከ300 እስከ 500 ዜጎች ማዕድ እንዲጋሩ ይደረጋል። በተከታታይ በሚደረጉ የአምሥት የበጎ ፈቃድ፣ የአምራችነት፣ የሰላም፣ የአገልጋይነት እና የአንድነት ቀናት በሚደረጉ የማዕድ ማጋራት መርሐግብሮች በድምሩ ከ130 ሺህ በላይ ዜጎች ማዕድ ማጋራት መርሐግብር ይካሄዳል።

በበጀት ዓመቱ ግብረ ሰናይ ድርጅቶችን፣ የአዲስ አበባ ከተማ ባለሃብቶችን እና የመንግሥት መዋቅሩን በማስተባበር የሕብረተሰቡን መሠረታዊ ችግሮች ሊቀርፉ ይችላሉ በተባሉ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንደተሠራም አቶ ሙሰማ አብራርተዋል።

ከዚህ በፊት የነበረውን ጦርነት መነሻ በማድረግ ለመከላከያ ሠራዊት እና በጦርነት ለተጎዱ አካላት ከፍተኛ የሆነ ሃብት የማሰባሰብ ሥራ በኮሚሽኑ አስተባባሪነት ሲከወን መቆየቱን ገልፀው፤ በተካሄደው ዘመቻ ወደ 57 ሺህ ዩኒት ደም ማሰባሰብ ተችሎ እንደነበር ገልፀዋል።

በተመሳሳይ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብርም እንደ አንድ ዋና የትኩረት ነጥብ ሆኖ ዓምና በክረምትና ዘንድሮም በበጋዎቹ ወራት ችግኞችን የመንከባከብና የመትከል ሥራዎች ተከናውነዋል ያሉት አቶ ሙሰማ፤ በዘንድሮው ዓመት ከ1 ነጥብ 1 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች የተሳተፉበት የአረንጓዴ አሻራ መርሐግብር መከናወኑን አስረድተዋል።

# ትህነግ በተፈናቃይ..

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በየመንደሩ ተደብቀው የሚገኙ የጥፋት ኃይሎችን ለማደን የቤት ለቤት ፍተሻ መጀመሩን ዶክተር ዳዊት ተናግረዋል።

በተከናወነው የፀጥታና ደህንነት ስራ ህጋዊ መታወቂያ ያልያዙ ግለሰቦች፣ ህገወጥ መሳሪያ ይዘው የተገኙና ከሽብር ቡድኑ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ሰርጎ ገቦች መያዛቸውን ገልጸዋል። ከተያዙት ሰርጎገቦች መካከል አራት የአሸባሪው ሕወሓት ታጣቂዎች መገኘታቸውን ዶክተር ዳዊት ተናግረዋል።

ተጠርጣሪዎቹን ለመያዝ የጸጥታ ኃይሉ ከሚያከናውነው የ24 ሰዓት ጥበቃ ባለፈ የህብረተሰቡም ጥረት ጉልህ አስተዋጽኦ አለው ያሉት ዶክተር ዳዊት፤ ህብረተሰቡም አካባቢውን ነቅቶ በመጠበቅ የሚያከናውነውን የጸጥታ ስራ አጠናክሮ እንዲቀጥል መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሰሞኑን ሾልኮ የወጣው የትህነግ ሚስጢራዊ ሠነድ በቀጣይ የሽብር ቡድኑ ሊከተላቸው ያሰባቸው አገር የማፍረስ ሴራዎቹ ተጋልጠዋል። "በዚህ ሰነድ ላይ በግልጽ እንደተጠቀሰው "ወደ አማራ ክልል በተፈናቃይ ስም ኃይል ማስገባት አለብን" ይላል።

ወደ አማራ ክልል በተፈናቃይና በተጓዥ ስም የሚገባ ኃይል ሊዘጋጅና ሥራውም በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊፈጸም ይገባል" ይላል የትህነግ ሚስጢራዊው ሰነድ።

ይህ ወደ ክልሉ የሚገባው ኃይል በተቻለው መጠን የትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቅሞ ወደ አዲስ አበባ ዙሪይም ሊጠጋ ይገባል የሚለው ይህ ሰነድ፤ " አስርገን የምናስገባው ኃይል በየደረሰበት አካባቢዎች መረጃና ሁኔታ የሚጠቁሟቸው አመራሮች ይኖራሉ" ሲልም ነው የገለጸው።

ወልዲያ በተረጋጋ መደበኛ እንቅስቃሴ ውስጥ ስትሆን፤ በከተማዋ የነዳጅ ኤለክትሪክና ስልክና የከተማዋ ውስጥ ትራንስፖርት አገልግሎቶች እየቀረቡ ይገኛል። የውሃ አገልግሎት ላይ አሁንም ችግር እንዳለ የከተማዋ ነዋሪዎች ገልጸዋል። በከተማዋ የሚገኙ ባንኮች በመደበኛነት አገልግሎቶች እየተሰጡ መሆኑን የኢፕድ ዘጋቢዎች ተመልክተዋል።

# የአሸባሪው ትህነግ....

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሥራውን ተረጋግቶ እንዲሰራ መቀሌ የገቡ ወታደሮችን አስወጥቷል ያሉት አቶ ብናልፍ፤ ሰብዓዊ ድጋፍ ለሚያደርጉ አካላትም መንገዱን ክፍት አድርጓል ብለዋል።

ሆኖም በመንግሥት በኩል ጦርነቱን ለማስቆም እና ሰላማዊ እልባት ለመፈለግ የተደረጉ ጥረቶች በሕወሓት በኩል እንቅፋት እንደገጠመው አብራርተዋል።

መንግሥት የሰላም ውይይቱን በአስቸኳይ ለመጀመር የሚያስችል የሰላም ምክረ- ሃሳብን፣ የያዘ ሰነድ ማዘጋጀቱን ይፋ ቢያደርግም፣ ሕወሓት በተቃራኒው፣ የተኩስ አቁም ስምምነቱን ማፍረሱ በግልጽ "ኃይል ብቸኛ አማራጩ" እንደሆነ ያሳያል ሲሉም ጠቁመዋል።

ግጭቱ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ መንግሥት ለሰላም ዕድል ለመስጠት ተደጋጋሚ ሙከራዎችን ሲያደርግ ቆይቷል ያሉት ሚኒስትሩ፣ የሰላም አማራጩን በዘላቂነት እውን ለማድረግና በሰሜኑ የትግራይ፣ የአፋርና የአማራ ክልል አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎችን ከገጠማቸው ችግር ለማላቀቅ የሕወሓት ታጣቂ ቡድን ጠብ አጫሪነቱን ሊገታ ይገባል ብለዋል።

አቶ ብናልፍ እንዳሉት፤ በአሁኑ ወቅት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል እየተከሰተ ያለው ግጭት ዋነኛው ምክንያት ለውጥን ለማደናቀፍና ላለመቀበል ካለ ጽኑ ፍላጎት ነው። በአንጻሩ በኢትዮጵያ የተሻለ ዴሞክራሲ፣ የተሻለ ፍትህ፣ የተሻለ ልማት ያለባትና የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት የተከበረባት ሀገር እንድትሆን በመንግሥት በኩል በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል።

መንግሥትም ይህን እውን ለማድረግ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል። ይህንን እውን ለማድረግ የተጀመረው ሰላማዊ እንቅስቃሴ ጥቅማችንን ጎድቶታል ብለው የሚያስቡ ኃይሎች አምርረው ለውጡን ይቃወሙ ጀመር። ከነዚህም ውስጥ ግንባር ቀደሙ ትህነግ ነው ብለዋል።

የትህነግ እንቅስቃሴ ለውጡን ብቻ መቃወም አይደለም፤ ሀገር በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ከአፍሪካ ሀገራት ብሎም ካደጉት ሀገራት ተርታ እንዳትሰለፍ የማድረግ ሥራ ነው። ይህ ሙከራው እንዳልተሳካለት ባወቀ ጊዜ ትግራይ ክልል በመሄድ በየቀኑ የጦርነት አዋጅና ትርኢቶች ሲያደርግ ቆይቷል ሲሉም ገልጸዋል።

መንግሥት ይህ እንቅስቃሴ አዝማሚያው ጥሩ አይደለም፤ ሀገሪቱን ወደ ጦርነት ይከታታል፤ ካለፈው የጦርነት ጊዜያት መማርና ማረም አለብን፣ አለበለዚያ ከበፊቱ የባሰ ሀገሪቱን ወደ ቀውስ ይከታታል በሚል ሕወሓት ከዚህ እንቅስቃሴ እንዲቆጠብ ተደጋጋሚ የሠላም ጥሪ ማቅረቡንም አስታውሰዋል።

መንግሥት በተደጋጋሚ ይሄን ጉዳይ በሠላም እንዲፈታ ጥረት ሲያደርግ ነበር ያሉት አቶ ብናልፍ፣ ይህ ጥረት በመንግሥት ብቻ ሳይሆን በሀገር ሽማግሌዎች፣ በሃይማኖት አባቶች፣ በእናቶችና ከኢትዮጵያ ውጪ በሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጭምር ወደ ጦርነት ሳይገባ ችግሩን በሠላም እንፍታ የሚል ጥያቄ ቀርቧል። ምክንያቱም በሠላም የማይፈታ ጉዳይ ምንም ነገር የለም። ይህም በጥሪ ብቻ አልነበረም በአካል መቀሌ ድረስ ተሂዶ ተሞክሮ ነበር ብለዋል።

ምላሹ ግን የፈለገ ነገር ይምጣ፣ ወደ ጦርነት እንገባለን የሚል ነበር ያሉት ሚኒስትሩ፤ በዚህም ጥቅምት 24ቀን 2013ዓ.ም ቡድኑ በሰሜን እዝ ላይ ጥቃት ፈጽሟል ሲሉ አስታውሰዋል። ይህ ደግሞ ግልጽ የሆነ የሀገር ሉአላዊነት መዳፈር ነው። ምክንያቱም መከላከያ ማለት የሀገር ሉአላዊነት የመጨረሻው ምሽግ ነው። በውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጪም የሀገሪቱ ሉአላዊነት የሚዳፈር አካልን ዋጋ የሚሰጠው መከላከያ ሰራዊት ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በዚህም መንግሥት የህግ ማስከበር ዘመቻ አድርጓል ያሉት የሠላም ሚኒስትሩ፣ የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች ጦርነቱን እንደምክንያት ተጠቅመው የተለያዩ የማጥቃት እንቅስቃሴዎች ሲያደርጉ ቆይተዋል። ነገር ግን በኢትዮጵያውያን በተባበረ ክንድ ይህን እንቅስቃሴ ማቆም ተችሏል።

በዓለም ላይ የተካሄዱ ጦርነቶች አሸናፊና ተሸናፊ ያልነበራቸው ውጤታቸውም ውድመት፣ ኪሳራና፣ በሀገራት ላይ ከፍተኛ ቀውስ ያስከተለ እንደሆነ የተናገሩት አቶ ብናልፍ፤ የአሸባሪው ትህነግ ሶስተኛ ዙር ጦርነት የተሰጠውን ተደጋጋሚ የሰላም እድል ያመከነበት እንደሆነም ጠቁመዋል።

አቶ ብናልፍ እንዳሉት፤ የአሸባሪው ትህነግ የጦርነት ጥሪ ትውልድን የማጥፋት ዘመቻ መሆኑ ግልጽ መሆን አለበት። "ጦርነትን እንደ ጀብድ ለሚያዩና ህዝብን ለማስጨረስ ጦርነትን የሚጎስሙ የቡድኑ መሪዎች ወደልቦናቸው ተመልሰው ቆም ብለው ሊያስቡ ይገባል" ብለዋል።

እንደ ሀገር ችግሮችን በውይይት መፍታት የሚያስችሉ መድረኮች እየተዘጋጁ ባሉበት በአሁኑ ወቅት ጦርነትን እንደተሻለ አማራጭ ለመጠቀም መሞከር ህዝብን የሚጎዳና ኃላፊነት የጎደለው አካሄድ መሆኑን ጠቅሰው፣ የሽብር ቡድኑን በተለያየ መንገድ የሚደግፉ አንዳንድ የምዕራባውያን ሀገራትም ከተሳሳተ መንገዳቸው በመውጣት የሽብር ቡድኑን ጸብ አጫሪነት ሊያወግዙ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በጠረጴዛ ዙሪያ ተነጋግሮ ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ ጦርነትን የመረጠው አሸባሪው ትህነግ ለሦስተኛ ዙር ጦርነት የትግራይን ህዝብ ከህጻን እስከ አዋቂ መመልመሉ ተገቢነት የሌለውና ሰብዓዊነት የጎደለው ተግባር ነው ብለዋል።

የአሸባሪው ህወሓት ትንኮሳ ቢኖርም መንግሥት እየተከተለ ያለውን የሰላም አማራጭ እንዳጠናከረ የጠቆሙት ሚኒስትሩ፣መንግሥት ከሰጠው ተደጋጋሚ የሰላም እድል ለመጠቀም የትግራይ ህዝብ አሸባሪውን ትህነግ ከድርጊቱ ሊያስቆመው እንደሚገባም አሳስበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሕወሓትን የአሸባሪነት ባህሪና የጥፋት ዕቅድ ያጋለጠው የሽብር ቡድኑ ሰነድ!

ከውልደቱ ጀምሮ የመጣበት የጥፋት እና የሽብር መንገድ ሕወሓትን አሸባሪ ብሎ ለመፈረጅ በቂና ከበቂ በላይ ቢሆንም ሰሞኑን የተገኘው ድብቅ ሰነድ ቡድኑ የቱን ያህል ከሽብር ለማትረፍ የተፈጠረና ለዚህ የሚሆን ፍጥረታዊ ስብእና የተላበሰ ስለመሆኑ በተጨባጭ ያመላከተ ሆኗል።

ቡድኑ በሕዝባዊ እንቢተኝነት የተነጠቀውን ስልጣን ፤ሀገርን በሽብር አዙሪት ውስጥ በመክተት መልሶ በእጁ ለማስገባት የትግራይን ሕዝብ የመቆመሪያ ካርዱ ከማድረግ ባለፈ ፤መላውን ሕዝባችንን በተጠና ሽብር የቁማሩ አካል ለማድረግ አቅዶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ሰነዱ የአደባባይ ሚስጥር አድርጎታል።

መላውን ሕዝባችንን ሰላም በመንሳት ፤ ሃገርን ከዳር እስከ ዳር በማሸበር ላይ የተመሰረተው የቡድኑ የጥፋት ስትራቴጂ፤ ራሱ በየአካባቢው ከሚያሰርጋቸው አሸባሪዎች በተጨማሪ ፤ በሃገር ውስጥ በአሸባሪነት የተፈረጀውን ሸኔን ጨምሮ ሌሎች ጽንፈኛ ቡድኖችን አካቷል። በዓለም አቀፍ ደረጃ በሽብርተኝነቱ የሚታወቀውን አልሸባብን በግልጽ የተልዕኮው አካልም አድርጓል።

በሕዝብ ላይ ሽብር፣ ፍርሃትና የስነ ልቦና ጫና መፍጠር፣ ለዚህ የሚሆኑ መረጃዎችን በሃገር ውስጥና በውጭ ሚዲያዎች መልቀቅን የስትራቴጂው አካል አድርጉ በሰነዱ ላይ ያስቀመጠው አሸባሪው ሕወሓት፤ ባለቤቶቻቸው አዲስ አበባ የሚገኙ ሚዲያዎችና ዩቲዩብ ቻናሎች የመረጃና የፋይናንስ ድጋፎችን በመስጠት የሽብር ዘመቻው አካል እንዲሆኑም በሰነዱ አቅጣጫ አስቀምጧል።

መንግሥት በችግር ጊዜ ውስጥ ሆኖ በሁሉም ዘርፍ ያገኘውን ስኬትም ሆነ በአጠቃላይ በኢኮኖሚ ዘርፍ ያገኘውን ልእልና አደናቅፎ ወደ ኋላ መመለስ ፤ በዚህም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንደመሪ ያገኙትን “ጊዚያዊ አንፃራዊ “ ያለውን መረጋጋት መንሳት የስትራቴጂው አካል አድርጎታል፤ ሕዝብ በማንቀሳቀስ የተጀመረው የእርሻ ልማት፣ ስንዴና ሌሎች የኢኮኖሚ ሥራዎች ማደናቀፍ ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚያስፈልግም ዘርዝሯል።

መንግሥት የጀመረውን የልማት ሥራዎችን ትቶ እሳት ማጥፋት ላይ እንዲጠመድ በሚልም የእርሻ ዘርፉ እንዲደናቀፍ በየአካባቢው ግጭት በመቀስቀስ እና ግጭት ለመቀስቀስ የሚያስችሉ ኃይሎች በማገዝ እረፍት በመንሳት እንደሚያስፈልግ በማተት፤ ይህም አሁን ለሶስተኛ ጊዜ ለጀመረው ወታደራዊ ዘመቻ ትልቅ ጥቅም እንዳለውም አስቀምጧል።

የአማራ ክልል በተወሰነ መልኩም ቢሆን ፊቱን ወደ ልማት ማዞሩ እንደ ትልቅ ስጋት በማየትም፤ይህ ኃይል የእርሻ ውጤቱን ወደ ቤቱ እንዲያስገባ ልንፈቅድለት አይገባም። ለጦርነት ባልተዘጋጁበት አሁናዊ እውነታ አስፈላጊ የሚባል ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል ሲልም ለአማራ ህዝብ ያለውን ጠላትነት በድጋሚ ግልጽ አድርጓል ።

በሀገሪቱ የሚነሱ የወሰንና የማንነት ጉዳዮችን ወደማያባራ ፖለቲካዊ ማህበራዊ ችግር በመለወጥ ፤የሽብር እቅዱ ማስፈጸሚያ ማድረግ እንደሚገባ፤ ሕዝብ እንዲያምጽና ፈጣን የስርአት ለውጥ እውን እንዲሆን ኢኮኖሚውን ማቃወስ ለነገ የማይባል ሥራ እንደሆነ በሰነዱ አጽንኦት ሰጥቶታል።

ለዚህም የተመረጡ አምራች ድርጅቶችንና መጋዘናቸውን ማጥቃትና ማፍረስ፣ ከእርሻ እስከ ገበያ ባለው ሂደት የዕለት አስቤዛ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እንዲኖረው ማድረግ፣ ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦች እና ነዳጅ እንዲስተጓጎል ዋና ዋና የማስገቢያ ኮሪደሮች በመቆጣጠርና ሌሎች እርምጃዎችን በመውሰድ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ችግር እንዲፈጠር እና እንዲባባስ ማድረግ እንደሚገባም አመላክቷል።

ይህ ሁሉ የጥፋት ቡድኑ የጥፋት ሀሳብና ሀሳቡን ለማስፈጸም የተገመዱ ሴራዎች ቡድኑ የቱን ያህል ከጥላቻና ጥፋት ውጪ ማሰብ የማይችል ፤ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ የትኛውንም ኃይል ሃገር የማፍረስ ትልሙ መቆመሪያ ካርድ ከማድረግ የማይመለስና ከዚህ ውጪ ለማሰብ የሚያስችል ምንም አይነት ስብእና እንደሌለው ያመላከተ ነው።

ትናንት በፍትህና ነጻነት ስም፤ ዛሬ ደግሞ ተከበሃል በሚል አዲስ ትርክት በትግራይ ሕዝብ ስም እየማለና እየተገዘተ ሕዝቡን ተነግሮ ለማያልቅ መከራና ስቃይ የዳረገውን ያህል፤ ዛሬ ደግሞ መላው ህዝባችን በብዙ መስዋዕትነትና ተስፋ አምጦ የወለደውን ለውጥ ሊያጨናግፍና ሃገር ሊያፈርስ ቀን ከለሊት እየተጋ መሆኑን በሰነዱ አረጋግጧል።

ይህ አደባባይ ላይ የተሰጣው የሽብር ቡድኑ ሃገር አሸብሮ ወደ ስልጣን የመመለስ ቀቢፀ ተስፋ ፤በየትኛውም መንገድ በዚህች ሀገርና ሕዝቦች ላይ ሊሰለጥን የሚችልበት ዕድል ባይኖረውም ፤እውነታውን ግን ሁሉም ዜጋ በሰከነ አእምሮ ሊያጤነውና ጥንቃቄ ሊያደርግበት የሚገባ ነው።

እያንዳንዱ ዜጋም የሽብር ቡድኑ በየአቅጣጫው በዘረጋው የጥፋት መረብ ተጠልፎ ፤ብዙ ዋጋ ከፍሎ ያመጣው ለውጥ ተጨማሪ ዋጋ እንዳይጠይቀው ፤የሚሄድባቸውን መንገዶች በጥንቃቄ መርገጥ ፤ ከሁሉም በላይ የቡድኑን ፍጥረታዊ ሽብርተኛ ማንነት ጠንቅቆ በመረዳት በሁሉ መስክ ሴራውን ሊያከሽፍ ይገባል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## ደጀንነትን በማጠናከር እና የመረጃ ስርጭትን በመግራት ...

**ፒያንኪ ዘኢትዮጵያ**

አሸባሪው ሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) የሰላም አማራጮችን ባለመቀበል ሦስተኛ ዙር ወረራ ፈጽሟል። በወረራ በያዛቸው አካባቢዎችም መገለጫው የሆነውንና የለመደውን ግድያ፣ ዝርፊያና ውድመት እየፈጸመ ይገኛል። መንግሥትም ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት አሁንም ቁርጠኛ እንደሆነና የዜጎችን ደህንነት እንዲሁም የሀገርን አንድነት የማስጠበቅ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመግለፅ የሰላም እጆቹን ሳያጥፍ ወረራውን የመቀልበስ ስራ እየሰራ ይገኛል።

ታዲያ የቡድኑን ወረራ ለመቀልበስና ሰላም ለማስፈን የሚከናወኑ ተግባራት ስኬታም ይሆኑ ዘንድ በጥምረት ሆኖ ወረራውን በጀግንነት እየመከተና እየቀለበሰ የሚገኘውን የጸጥታ ኃይል መደገፍና ማጠናከር ወሳኝ ግብዓት ነው። በዚህ ረገድ ትኩረት የሚሹ ጥቂት ጉዳዮችን በዝርዝር መመልከት ያስፈልጋል። ሕዝቡና መንግሥት ለጸጥታ ኃይሉ የሚያደርገው ድጋፍ በተለያዩ መልኮች ሊገለገጽ የሚችል የደጀንነት ተግባር ነው። ምግብና መጠጥ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ማቅረብ፣ ደም መለገስ፣ በሞራል ማበረታታት ... ድጋፉ ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል ይጠቀሳሉ።

ሕዝቡ ከዚህ ቀደም በተካሄዱት የሕግ ማስከበር እና የህልውና ዘመቻዎች ለጸጥታ ኃይሉ ያደገው ድጋፍ እጅግ የሚደነቅ እንደነበር ታይቷል። ምግብና አልባሳትን አቅርቧል፤ ቁስለኞችን ተንከባክቧል፤ የጸጥታ ኃይሉን በሞራል አበረታትቷል፤ ከሠራዊቱ ጋር ተሰልፎም ተዋግቷል፤ በአጠቃላይ ሕዝቡ ያለውን ሁሉ ሳይሰስት ሰጥቷል። የጸጥታ ኃይሉ ስለሕዝቡ ደጀንነት የሰጠው ምስክርነት የሚዘነጋ አይደለም። ይህ የሕዝቡ ደጀንነትም የሕግ ማስከበርና የህልውና ዘመቻዎቹ በድል እንዲጠናቀቁ አስችሏል።

ታዲያ አሁንም ጥምር ጦሩ ሕወሓት የከፈተውን ወረራ በመቀልበስ አስተማማኝ ድል እንዲያስመዘግብ ሕዝባዊ ደጀንነቱ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ሕዝቡ በአሉባልታዎች ተደናግጦ አካባቢውን መልቀቅ የለበትም። ከዚህ ቀደም ለጸጥታ ኃይሉ ሲያደርግ የነበረውን ድጋፍ አሁንም አጠንክሮ ማስቀጠል አለበት። በጦርነቱ ቀጠና ውስጥ ከሚገኘው ሕዝብ በተጨማሪ በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚገኘውም ሕዝብ ለጸጥታ ኃይሉ ድጋፍ በማድረግ ደጀንነቱን ማረጋገጥ ይገባዋል። በእርግጥ በጦርነቱ ቀጠና ውስጥ ያለው ሕብረተሰብ አሁንም ለጸጥታ ኃይሉ ደጀንነቱን በተግባር እያስመሰከረ ነው። ይህ ደጀንነት ሀገር አቀፍ ሆኖ አሁን ካለው የበለጠ መጠናከር አለበት።

የመረጃ ፍሰት አመራርና አስተዳደርም ሌላው በጥብቅ ሊታሰብበትና ችላ መባል የሌለበት ጉዳይ ነው። ከኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ አንፃር የመረጃዎች ተደራሽነት ጥንቃቄ ይፈልጋል። መንግሥት፤ ሕወሓት የከፈተውን ወረራ ለመቀልበስ ምላሽ መስጠት ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ በአንዳንድ «አክቲቪስት» ተብዬዎች ዘንድ የሚታየው መረን የለቀቀ የመረጃ አያያዝና አሰጣጥ ጉዳይ የሚያስደነግጥና የሚያሳፍር ነው።

«የመረጃ ባለቤት ነን» ብለው መረጃ የሚያቀርቡ እነዚህ ግለሰቦችና ቡድኖች ከመረጃ አያያዝና አቀራረብ ሥርዓት ጋር የማይተዋወቁ፣ የውሸት መረጃ በማሰራጨት የተካኑ እንዲሁም የመረጃን ትርጉምና አስፈላጊነት የማያውቁ ናቸው። የእነዚህ «አክቲቪስቶች» መረጃዎች በውሸት የታጨቁ፣ ብሔራዊ ጥቅምንና ወቅታዊ ሁኔታን ከግምት ውስጥ ያላስገቡ እና ማሕበረሰባዊ እሴቶችን የጣሱ የጥራዝ ነጠቆች ፕሮፓጋንዳዎች ሆነው ታዝበናል።

ሕወሓት የከፈተውን ወረራ ለማስቆም የሚደረገውን ዘመቻ በተመለከተ በአንዳንድ አክቲቪስቶች በኩል የሚቀርቡት መረጃዎች ለሕወሓት ወታደራዊ ዘመቻ አጋዥ የሆኑና የሕዝብንም ሆነ የሀገርን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ ሆነው ይስተዋላሉ። የአክቲቪስቶቹ መረጃዎች አብዛኞቹ በሀሰተኛ ዜናዎች የተሞሉ ናቸው። የጥምር ጦሩን እንቅስቃሴና ብዛት ይፋ የሚያደርጉ ብዙ «አክቲቪስት» ነን ባዮችም አሉ። ሕዝቡ ተደናግጦ አካባቢውን እንዲለቅ ምክንያት ሲሆኑ ተስተውሏል። ሠራዊቱ የሚጓዝበትን አካባቢ በፎቶ ጭምር እያስደገፉ በማሕበራዊ ሚዲያዎች የሚያሰራጩ አካላት በዋጋ የማይተመን ውድ መረጃ ለሕወሓት አሳልፈው እየሰጡ እንደሆነ አያውቁም ማለት ሞኝነት ነው፤የሕወሓት ተባባሪዎች ናቸው ብሎ ማሰብም ሞኝ አያስብልም።

ይህ የባንዳነት ተግባር የሚታይበት የ «አክቲቪስቶች» የመረጃ ስርጭት ተግባር፤ ለሕወሓት ዓለም አቀፋዊ ወዳጆች የሐሰት ዘመቻ ግብዓት ሆኖ ያገለግላል። በኢትዮጵያ ላይ የሐሰት ዘመቻ የከፈቱ የሕወሓት ወዳጆች የእነዚህን «አክቲቪስቶች» መረጃ በመያዝ መንግሥት ፀብ ጫሪ እንደሆነ አድርገው ስም ማጥፋታቸውን ተያይዘውታል። ብዙዎቹ ዓለም አቀፍ (የውጭ) መገናኛ ብዙኃንና ዓለም አቀፍ ተቋማት ስለሕግ ማስከበሩም ሆነ ስለሕልውና ዘመቻው የሚያሰራጩት ዘገባ በእውነተኛ መረጃ ላይ ያልተመሰረተ፣ ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያላስገባና ተገቢ ያልሆነ ፀረ-ኢትዮጵያ ዘመቻ እንደነበር ይታወሳል።

ይህም ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ስለጉዳዩ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዝ (እንዲኖረው) ከማድረጉ ባሻገር የኢትዮጵያ ጠላቶች «ኢትዮጵያን ለመበታተን ከዚህ የተሻለ ጊዜ/እድል አናገኝም» ብለው ታጥቀው እንዲነሱና በረጅም ጊዜ ታሪኳ ከጦርነት ይልቅ ሰላምን፤ ከኃይል ይልቅ ንግግርን ለማስቀደም እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ትብብርንና ወንድማማችነትን የሚያሰፍኑ አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት እንዲመሰረቱና እንዲጠነክሩ ባላት ቁርጠኛ አቋም የምትታወቀው ኢትዮጵያ ስሟ እንዲጠለሽ በር ከፍቶ እንደነበርም የሚዘነጋ አይደለም።

በሌላ በኩል ሕ.ወ.ሓ.ት በተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ ባሉ አጋሮቹ በኩል አገሪቱ ልትበታን እንደሆነና የፌዴራሉ መንግሥት በትግራይ ሕዝብ ላይ ጦርነት እንዳወጀ አስመስሎ በርካታ የውሸት መረጃዎች እንዲሰራጩ አድርጓል። እነዚህን መረጃዎች ያዳመጡና የተመለከቱ ብዙ የውጭ አገራት ሰዎችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ደግሞ መረጃዎቹን እንደወረዱ በመቀበል ከእውነት የራቀ ድምዳሜ ላይ ሲደርሱ ተስተውለዋል። አንድ ጊዜ ተንታኝ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ጋዜጠኛ፣ ሲያሻቸውም አማካሪ ወይም ተማራማሪ ሆነው የሚንቀሳቀሱት እነዚህ የሕወሓት ወዳጆች፤ ወረራውን የመቀልበስ ስራውን አደጋ ላይ የሚጥሉ መረጃዎችን የሚያሰራጩ «አክቲቪስቶች»ን መረጃ በመያዝ የለመዱትን ቅጥፈታቸውን ቀጥለውበታል።

መንግሥት የመረጃ ፍሰቱ ጉዳዩን በሚመለከተው አካል ብቻ ይከናወናል ብሎ ቢያሳውቅም፤ እንዲህ ዓይነት አደገኛ መረጃዎችን በሚያሰራጩ አካላት ላይ ቁጥጥር እያደረገ ግን አይመስልም። ወረራውን ለመቀልበስ የሚደረገውን ጥረት አደጋ ላይ የሚጥሉ መረጃዎችን የሚያሰራጩ ግለሰቦችና ቡድኖች በግልጽ እየታወቁ ሳለ፤ እንዲህ ዓይነት ሀገርን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ መረጃዎችን ሲያሰራጩ «እንዲያው ሕጋዊ እርምጃ መወሰዱ ይቅርና ኮስተር ባለ ዓይን የሚያያቸው አንድም የመንግሥት አካል የለም እንዴ?» ያስብላል።

መላው ኢትዮጵያዊ ለቡድኑ የጥፋት ተልእኮ ተገቢውን ትኩረት ሊሰጥ ይገባል። በዚህ በኩል ምንም አይነት ብዥታ ሊኖር አይገባም ። በአሁኑ ወቅት በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል ያለው የሀገሪቱ ሕዝብ ለጥፋት ሃይሉ የሰጠው ትኩረት እኩል ነው ለማለት አያስደፍርም። ብዙ ሰው ሀገሪቱ እጅግ ዘግናኝ ወንጀሎችን ከሚፈጽም እንዲሁም የግዛት አንድነቷን ለማሳጣት ቆርጦ ከተነሳ ሀገር አፍራሽ ቡድን ጋር እየተፋለመች እንደምትገኝ በአግባቡ የተረዳ ፤አንዳንዱም እውነታውን ትኩረት ሰጥቶ የሚከታተል አይመስልም።

አሸባሪው ቡድኑ የአማራና የአፋር ክልሎች ብቻ አደጋ ተደርጎ መቆጠር የለበትም። በእርግጥ የክልል መንሥታት ሕወሓት የፈጸመውን ወረራ ማውገዛቸውና ወረራውን ለመቀልበስ አስፈላጊውን ትብብር እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፤ሕዝብን አስተባብሮ ይህን የአጋርነት መልእክት ወደ ተግባር መለወጥም ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ችግር የሚወገደው በመላው ኢትዮጵያዊ ትብብር መሆኑ መዘንጋ የለበትም። በአጠቃላይ ሕወሓት የከፈተውን ወረራ ለመቀልበስና ድል ለማስመዝገብ ሁሉም ሕብረተሰብ ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጥ በማድረግ ሕዝባዊ ደጀንነትን ማጠናከር እጅግ አስፈላጊ ነው!

# ነፃ ሃሳብ

## አሸባሪው ሕወሓት የመንግስትን የሰላም እጆች ለምን ረገጠ?

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

መንግስት ኢትዮጵያ ሰላም፣ እርቅ እና አንድነት ብቻ እንደሚያስፈልጋት በማመን ለሰላም ድርድር ያልከፈለው መስዋዕትነት የለም። ለአገራችን ሰላም፣ ለህዝቡም ደህንነት ሲል ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር ለመደራደር ይሁንታ ከማሳየትም በላይ፣ ድርድሩን ያለ ቅድመ ሁኔታ የትም፤ መቼም ለማካሄድ ፈቃደኝነቱንም አስታውቋል።

ይሑንና ሽብርተኛው ቡድን ይሄን የመንግስት የሰላም ጥሪ ከመቀበል ይልቅ በትግራይ ወጣቶች ደም ከንቱ ህልሙን ለማሳካት ለሶስተኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ከፍቷል። በተግባሩም ለሰላም ደንታ ቢስ ስለመሆኑ በተጨባጭ አሳይቷል። ከሰላም ሳይሆን ከነውጥ ትርፍ ለማትረፍ መነሳቱን በገሃድ አስመስክራል።

አሸባሪው ሕወሓት በደደቢት በርሀ ውስጥ ወድቆ ሲበቅል መልካም ዘር ለመሆን ሳይሆን እኩይ ለመሆን ነበር። በርሀ እኮ ዘር የለውም። በርሀ እኮ መልካም ዘርን አያበቅልም። የበርሀ ተፈጥሮ አስጨናቂነት ነው።

ዛሬም እያራመደ ያለው በደደቢት በርሀ ውስጥ በገባው አገር የማፍረስና የራስ ወዳድነት መንገድ ነው። ይሕ ባይንማ ለአምስት አስርት አመታት ከጦርነት ያልወጣውን የትግራይ ህዝብ ለጦርነት ባልማገደው ነበር።

እንጂማ ከሰላም በቀር፣ ከልማት በቀር፣ ከአንድነት በቀር ምንም የማያሻትን ድሀ አገሩን በጦርነት አረርና በእዬዬ ዋይታ ሲኦል ባላደረጋት ነበር። ቡድኑ አላማው አገር መገንባት ቢሆን ኖሮ ለሀሳቡ እንደ ሰላም የሚያስፈልገው አልነበረም።

አላማው መልካም ነገር ቢሆን ኖሮ እንደ እርቅና፣ እንደ ድርድር የሚጠቅመው አንዳች አይኖርም ነበር። ግን አላማው አገርና ህዝብን መጥቀም ሳይሆን ራሱን መጥቀም ስለሆነ የሰላም አማራጮችን አልተጠቀመባቸውም። እየተዋጋ ያለው ደደቢት በርሀ ውስጥ ለገባለት በመግደል ስልጣን የመያዝ ሱስን እውነት ለማድረግ እንጂ መልካም አላማ ኖሮት እንዳይደለ የተራመደባቸው ሀያ ሰባት አመታት አመላካች ናቸው።

ቡድኑ ከታሪካዊ ጠላቶቻችንን ጋር ሳይቀር በማበር በአገርና በህዝባችን ላይ ይሄ ነው የማይባል ግፍና በደል ፈፅሟል። በይቅርታ የማይጠራ፣ በእርቅ የማይሽር ምህረት የለሽ ነውር ሰርቷል። ይሑንና መንግስት ለሰላም ዋጋ በመስጠትና ከሰላም የሚገኝን ትርፍ በማስላት ያለፈን በደል ይቅር ብሎ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለሰላም ድርድር እንቀመጥ ሲል ጠይቋል።

ቡድኑ ህዝባዊና አገራዊ አላማ የሌለው፤ አላማው አገር ማፍረስ፣ ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር አንድነትን መስርቶ የህዝቡን ክብር፣ የአገራችንን ሉአላዊነት መሻር በመሆኑ የሰላም ድርድሩን ለመቀበል ውስጡ አልፈቀደለትም።

ቡድኑ በአንድ ራስ ሁለት ምላስ እንዳለው የአገርኛ ብሂል ገጸ ባህሪ ነው። በህይወቱ አንድም ቀን ለራሱም ሆነ ለሚታገልለት ህዝብ እውነት ሆኖ አያውቅም። "ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሀል እንደሚባለው"አንዱን ምላሱን ለግፍ አንዱን ደግሞ ለተነካሁና ለእዬዬ ሲጠቀም የኖረ ነው። አሁንም በዚህ እውነት ውስጥ የቆመ ነው። እየገረፈ መጮህ ባህሪው ነው። ሳይዋሽ፣ ሳይሰርቅ የኖረበት ጊዜ የለም።

እየገደለ ሞትኩ እንዳለ ነው። እየጎዳ ተጎዳሁ ማለት ይችልበታል። በረጅም የፖለቲካና የስልጣን ዘመኑ እንዴትና በምን መልኩ ስልጣን ላይ እንደቆየ ቢመረመር ከውሸትና ከማስመሰል ሌላ መልስ አናገኝም። ለነገሩ የሕወሓት ታሪክ፣ ፖለቲካ፣ ርዕዮተ አለም ምርምር አይጠይቅም። ማንም ሊረዳው የሚችል ግልጽ የማጭበርበር ፖለቲካ ነው።

ሁሉን ትተን የዚህ ሳምንት ነውሩን ብናስታውስ እንኳን የአለም ምግብ ፕሮግራም ለሰብአዊ አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆን በመቀሌ ያከማቸውን ነዳጅ ሰርቆ ‹‹አልሰረቅኩም ያበደርኩትን ነዳጅ ነው የወሰድኩት››ሲል አይኑን በጨው አጥቦ አስተባብሏል። እንዴት ነው በጦርነትና በብዙ ጉስቁልና ውስጥ ያለችው ትግራይ ለአለም የተራድኦ ድርጅት ነዳጅ የምታበድረው?

ሕወሓት አይደለም ለሌላው ለራሱም እውነት የሌለው ቡድን ነው። ከአንድ ሰፈር፣ ከአንድ ነገድ፣ በአንድ ጫካ ውስጥ ተሰብስበው የመሰረቱት ለህዝብ ሳይሆን ለራስ፣ ለአገር ሳይሆን ለቡድን፣ ለትውልድ ሳይሆን ለብሄር የተቋቋመ ቡድን ነው። ይሄ ቡድን እውነት ቢኖረው እስካሁን ድረስ በአገርና ህዝብ ላይ ለፈጸማቸው በደሎች ይቅርታ ጠይቆ ወደሰላም ይመለስ ነበር።

ግን አላማው ሰላም ስላልሆነ ሰላምን አይመርጥም‹። አልመረጠምም። የሚፈልጋቸውን እኩይ ነገሮች በድርድር ሳይሆን በውድድር፣ በምክክር ሳይሆን በክርክር የሚያገኝ መስሎት እየገደለ ነው።

አላማውን የሚያሳካው በሰላም ውስጥ ሳይሆን በጦርነት ውስጥ ስለመሰለው በንጹሀን ሞት ለማትረፍ እየሞከረ ነው። የሕወሓትን ትላንትም ሆነ አሁናዊ ማንነት ለማወቅ በአገርና ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ስቃይና ኪሳራ ማየቱ ብቻውን በቂ ነው። የሰላም አማራጮችን ገፍቶ፣ የኢትዮጵያውያንን ስቃይ ችላ ብሎ በገዛ ወገኑ ላይ ጦርነት መክፈቱ ብቻ የቡድኑን አውሬነት በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል።

ቡድኑ ትላንትና በመግደል ውስጥ ነበር፤ ዛሬም በመግደል ውስጥ ነው። እጆቹ ከመግደል፣ ልቦናው ከማስጨነቅ አልቦዘነም። አውሮፓና አሜሪካ አስቀድሞ ኢትዮጵያን እንደሁለተኛ አገሩ የተቀበለ ቡድን ነው።

ኢትዮጵያን አገሬ፣ ህዝቡን ወገኔ ብሎ የመጥራት ወኔ የለውም። አይኖረውምም። የትኛውም አገር፣ የትኛውም ጠላት አገራችንን በሕወሓት ልክ አንገት ያስደፋት የለም። ኢትዮጵያ ብትጠፋ ግድ አይሰጠውም።

ሕወሓት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ግድ የሚሰጠው ቡድን ቢሆን ኖሮ ከአንድም ሁለት ጊዜ ለቀረበለት የሰላምና የድርድር አማራጭ ይጠቀም ነበር። ኢትዮጵያውያን ይሄን ቡድን ልንረዳው ይገባል።

ሕወሓት አላማው ጥፋት ብቻ ነው። እያጠፋ ያለውም የጋራ አገራችንን፣ የጋራ ታሪካችንን፣ የጋራ እሴታችንን ነውና በአንድ ላይ ልናወግዘው ይገባል። ትግራውያንም ቢሆኑ ይሄን ቡድን ተደግፈው የሚያተርፉት አንዳች ነገር የለም።

ያለፉት ሀያ ሰባት አመታት በሕወሓት አገዛዝ የትግራይ ህዝብ ምን ሁኔታ ላይ እንደነበር የምናውቀው ሀቅ ነው። የትግራይ ህዝብ ይሄን ቡድን ገፍቶ እስካልጣለና እስካልተቃወመ ድረስ ከሞትና ከጉስቁልና መቼም አይወጣም።

ቡድኑ ጥቂት ርህራሄ እና አዘኔታ ብሎም ሰብአዊነት የሚሰማው ቢኖረው ኖሮ ለትግራይ ህዝብ ሲል ቅድመ ሁኔታዎችን ሳይደረድር የሰላም አማራጩን ተቀብሎ እየሞተና እየተንገላታ ላለው የትግራይ ህዝብ ውለታ መዋል ይችል ነበር። ይሑንና የትግራይ ወጣት ሞትና እንግልት ግድ የማይሰጠው ስለሆነ ከጦርነት አስተሳሰብ አልወጣም።

አንድ ፖለቲከኛ፣ አንድ ቡድን፣ አንድ ጦረኛ እየሞተና እየተዋጋ ያለው በአላማና ለአላማ ከሆነ መጀመሪያ ሊያደርገው የሚገባው ነገር የሰላም አማራጮችን መፈለግና በተገኘው የሰላም አማራጭ ላይ መሳተፍ ነው።

ሕወሓት ግን አይደለም የሰላም አማራጮችን መፈለግ ቀርቶ ከፌደራል መንግስት የሚቀርብለትን የሰላም አማራጮች ጥላሸት እየቀባ መቼም በማያሸንፈው ጦርነት ውስጥ የትግራይ ወጣቶችን መማገድን ነው የተያያዘው። ሰላም የማይፈልግ፣ በሰላም አማራጮች ላይ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ያልሆነ ቡድን ከመግደልና ከማስገደል ባለፈ ምን አላማ ይኖረዋል?

**ቡድኑ ከታሪካዊ ጠላቶቻችንን ጋር ሳይቀር በማበር በአገርና በህዝባችን ላይ ይሄ ነው የማይባል ግፍና በደል ፈፅሟል። በይቅርታ የማይጠራ፣ በእርቅ የማይሽር ምህረት የለሽ ነውር ሰርቷል**

አገር በደም ጥማት ሱስ አትቆምም። አገር በመግደልና በማስገደል አትለማም። ሰላም በጠመንጃ አይመጣም። ሕወሓት ግን በዚህ ዘመኑን ባልዋጀ፣ ለዚህ ትውልድም ሆነ ለዚህ ዘመን በማይመጥን ድሮዋዊ እሳቤ ውስጥ ሆኖ በህዝብ መአበል እኩይ አላማውን እየፈጸመ ነው። የሰላም አማራጮችን እየዘጋ፣ የተኩስ አቁም ስምምነቶችን እየጣሰ፣ ኢትዮጵያ የምትዋረድበትን ጊዜ እየጠበቀ በደም ጥማት ሱስ በንጹሀን ላይ ሞትን ሲያውጅ ነበር።

ከመግደል ባለፈ ለሰላም የሚሆን ሙጣጭ አቅም በውስጡ የለም። ከዚህ አውሬአዊ ባህሪው በመነሳት ለምን አላማ እንደቆመ፣ በምን አላማ እየገደለና እያስገደለ እንዳለ መረዳት ይቻላል። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ለሚሞቱና ለሚገድሉ ነፍሶች ረፍት ይሆን ዘንድ መንግስት የሚሰጠውን የሰላም አማራጭ ችላ ብሎ እንቅፋት የሚፈጥረው ከምን ተነስቶ እንደሆነ መረዳት አይከብደንም።

ሕወሓት መቼም ኢትዮጵያዊ ሆኖ አያውቅም። ለታሪካዊ ጠላቶቻችን አሽከር በመሆን ለአመታት ሰርቷል። ዛሬም እየሰራ ያለው ይሄንኑ ነው። ኢትዮጵያን ማስጎንበስ፣ ህዝቦቿን ማዋረድ ለዘመናት የተካነው የክፋት ሃሳቡ ነው። ከኢትዮጵያ ላይ በዘረፈው ገንዘብ፣ በዘረፈው ጦር መሳሪያ ኢትዮጵያን እየጎዳ ነው።

ይሄ ቡድን እስካልተወገዘ ድረስ፣ ከታሪክ እስካልተሰረዘ ድረስ እኛም ሆንን አገራችን ታማሚ ናት። የሕወሓትን አላማ ተረድተን ስለ አገራችን ስንል ይሄን ቡድን በአንድ ላይ የምንፋለምበት ጊዜ አሁን ነው።

ይሄንን በእውቀት ሳይሆን በስሜት፣ በምክንያት ሳይሆን በራስ ወዳድነት እየገደለና እያስገደለ ያለ ቡድን ለመመከት ኢትዮጵያውያን አንድ መሆን ይጠበቅብናል። የትግራይ እናቶች ወልደው እንዲስሙ፣ ዘርተው እንዲቅሙ ወጣቶችም ከመሞት ወጥተው ከፍ ላለ ቁም ነገር እንዲበቁ ይሄን ነፍስ በላ ቡድን ከታሪካቸው መፋቅ ይኖርባቸዋል።

ሰላም ቅድመ ሁኔታ የለውም። የሰላም ቅድመ ሁኔታ ተነጋግሮ መግባባት ብቻ ነበር።አሸባሪዎች አላማቸው መግደል ስለሆነ አላማ ካላቸው ቡድኖች የሰላም አማራጮችን መስማት አይፈልጉም። በሕወሓትም የሆነው ይሄ ነው። መንግስት የሰላም አማራጮችን ሲሰጠው ሰበብ በመደርደር፣ ትንኮሳ በመፈጸም፣ ቅድመ ሁኔታዎችን በመዘርዘር የሰላም ጉዞውን ሲያደናቅፍ ነበር።

ብዙዎች ተስፋ የጣሉበት፣ የአገራችን የሰላም ጮራ የፈነጠቀበት የሰላም ድርድር እንኳን የከሸፈው በዚህ ቡድን ነው። ይሄም ቡድኑ ለሰላም ሳይሆን ለመግደልና ለማስገደል ብቻ እንደተፈጠረ የሚያሳይ ሁሉም ሊረዳው የሚችል ባህሪው ነው። በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ብዙ እዳ እያለበት መንግስት ግን ሰላምን መርጧል። መንግስት ለሰላም ያለው ቁርጠኝነት ዝም ብሎ ሳይሆን ምን ያክል የሰላምን ዋጋና አስፈላጊነት ከማወቅ የመነጨ ነው።

የትም መቼም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሰላምም መፈለግ ዝም ብሎ የሚታይ ነገር አይደለም። እውቀትና አስተውሎት የታከለበት የጠለቀ የመሻት ምስጢር ነው፤ ግን አልተጠቀመበትም። እንዲህ አይነት ልቦች፣ እንዲህ አይነት እሳቤዎች ለአገር ከመወገን፣ ለወገን ከመጨነቅ የሚመነጩ ናቸው። መንግስት በዚህ እውነት ላይ ተራምዶ ነው ከሕወሓት ጋር ለድርድር መቀመጥን የመረጠው።

የሕወሓት መራሹ ቡድን ግን መንግስት ያየውን የሰላም እድል ማየት አልቻለም። በሰላምና በመነጋገር ችግሮችን መፍታት እንደሚቻል ገና አልገባውም። መንግስት የጀመረውን የሰላም አማራጭ ጥላሸት መቀባቱም ከሰላም ይልቅ በጦርነት ውስጥ አላማውን ለማሳካት ስለሚመቸው ነው። እንዲሁም ደግሞ ኢትዮጵያን የማፍረስ አላማ ታጥቆ ስለተነሳ ነው። አገሩን የሚወድ ሁሉ ይሄን ቡድን ሊፋለመው ይገባል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ - የኢትዮጵያ ድርሻ

ዳግም ከበደ

ለሰው ልጆች ሥልጣኔና የዘመናዊነት መሻሻል ፈር ቀዳጅ የፈጠራ ውጤቶች ናቸው ተብለው ከሚታሰቡት ውስጥ በይነ መረብ (ኢንተርኔት) ዋንኛ ተጠቃሽ ነው። ዓለማችንን የሚመራው መረጃ ነው። ይህን ታላቅ ቁልፍ ሳይዛባና ትክክለኛውን እውነታ ሳይለቅ በሁሉም ስፍራ እንዲደርስ ደግሞ ሁነኛ መንገድ ያስፈልጋል። የሰው ልጆች እንደየ አካባቢያቸው ባህልና የአኗኗር ሁኔታ ደግሞ አንዱ ከአንደኛው ጠቃሚ መረጃዎችን ይለዋወጡ ነበር። ቀስ በቀስ ደግሞ እየዘመነና ቅርጹን እየለዋወጠ ፈጣን፣ የተጣራ እንዲሁም ጉልበትንና ወጪን የሚቀንስ "ዲጅታል" መረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል። የኮምፒውተርና የበይነ መረብ ቴክኖሎጂ በዓለማችን ላይ ከተዋወቀበት ጊዜ አንስቶ መረጃዎች ለፈለጋቸው ሁሉ በቅጽበት እንዲዳረሱና ጥቅም ላይ እንዲውሉ አስችሏል። ይህ ሂደት የበይነ መረብ ቋት ላይ ያለን መረጃ በተገቢው ማስተዳደር፣ ማዳረስ ብሎም ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ የሚል ፅንሰ ሃሳብ ይዞ ሊመጣ ችሏል።

የተባበሩት መንግሽሥታት ድርጅት የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ጉዳይ ክፍል በዓለም አቀፍ ደረጃ የበይነ መረብ አስተዳደር የምክክር ጉባኤ "the Internet Governance Forum (IGF)" እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ከ2006 ጀምሮ እንዲኖር ደንግጎ ባለድርሻ አካላት በፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ሕግና ደንብ ዙሪያ እንዲወያዩና በየጊዜው ሪፎርሞችን እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል።

**የበይነ መረብ አስተዳደር ምንነት**

የበይነ መረብ (የኢንተርኔት) አስተዳደር በመንግሥታት፣ በግሉ ሴክተር እና በሲቪል ማሕበረሰብ በየራሳቸው ሚና የጋራ መርሆዎችን፣ ደንቦችን፣ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን እና የበይነ መረብ ዝግመተ ለውጥ እና አጠቃቀምን የሚቀርጹ ፕሮግራሞችን ማዳበር እና ተግባራዊ ማድረግ ነው። ይህ ትርጓሜ የሰጠው "የቱኒዝ አጀንዳ ለመረጃ ማሕበረሰብ" እንዲሁም በመረጃ ማሕበረሰብ ላይ አተኩሮ 2005 በተካሄደው የዓለም ጉባኤ ላይ በተደረገ የአገራት ስምምነት ነው።

ከላይ በዝርዝር ለማንሳት እንደሞከርነው የበይነ መረብ (ኢንተርኔት አስተዳደር ፎረም) "IGF" ከኢንተርኔት አስተዳደር ቁልፍ አካላት ጋር በተያያዙ የሕዝብ ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ የብዙ ባለድርሻ አካላት የውይይት መድረክ ነው። እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2006 ከተካሄደው ከመጀመሪያው ስብሰባ ጀምሮ (አይ ጂ ኤፍ) በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሃፊ "በቱኒስ አጀንዳ ለኢንፎርሜሽን ሶሳይቲ" በተቀመጠው ትእዛዝ መሰረት በየዓመቱ ይጠራል። ፎረሙ የውይይት መድረክ እንደመሆኑ መጠን የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በእኩል መጠን መረጃ ለመለዋወጥ እና መልካም ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ ወደ ጠረጴዛው ያቀርባል። አይ ጂ ኤፍ የበይነ መረብ እድሎችን እንዴት ከፍ ማድረግ እና አደጋዎችን እና ተግዳሮቶችን እንዴት እንደሚፈታ የጋራ ግንዛቤን ያመቻቻል።

ምንም እንኳን የቱኒዝ አጀንዳ በሕጋዊ መንገድ አስገዳጅ ባይሆንም የዓለም አቀፍ ጉባዔ ስለ መረጃ ማሕበር ዓላማዎችን እና የድርጊት መስመሮችን በአገር አቀፍ፣ በክልላዊ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ትግበራን በተመለከተ ተከታታይ ምክሮችን ይዘረዝራል። ከእነዚህም መካከል ብሔራዊ ኢ-ስትራቴጂዎችን እንደ ሰፊው አገራዊ የልማት እቅዶች መገንባት፣ የሁለትዮሽ እና የባለብዙ ወገን የቴክኒክ ድጋፍ ፕሮግራሞችን በመጠቀም፣ የተባበሩት መንግሥታት የክልል ኮሚሽኖችን እና የተባበሩት መንግሥታት ኤጀንሲዎችን በአፈፃፀም ሂደት ውስጥ ማሳተፍ እና የሁሉም ባለድርሻ አካላት በአፈጻጸም እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳትፎን ያካትታሉ። ለምሳሌ በ2015 የዓለም አቀፍ ጉባዔ ስለ መረጃ ማሕበር ውጤቶች አፈጻጸም አጠቃላይ ግምገማም ተጠርቶ ነበር። አጀንዳው በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ከሚያዝያ 2006 ባወጣው ውሳኔ 60/252 ጸድቋል።

እ.ኤ.አ በታህሳስ 2015 የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ከፍተኛ ደረጃ ስብሰባ በኒውዮርክ ተካሂዶ ነበር። በቱኒዝ አጀንዳ በሚፈለገው መሰረት የዓለም አቀፍ ጉባዔ ስለ መረጃ ማሕበር ውጤቶችን አፈጻጸም ለመገምገም ወስኗል። ስብሰባው የተጠናቀቀው በመንግሥታት መካከል የተስማማበት የውጤት ሰነድ በማጽደቅ ከሌሎች ጋር በቱኒዝ አጀንዳ ውስጥ የተቀመጡትን ቃላቶች በማረጋገጥ፣ ባለፉት 10 ዓመታት የተመዘገቡ ለውጦችን በማረጋገጥ፣ የዲጂታል ክፍፍልን በማገናኘት እና በማጠናከር ረገድ የበለጠ ጥረት እንዲደረግ በመወሰንና ምክረ ሃሳብ በመስጠት ነበር። በዓለም አቀፍ ጉባዔ ስለ መረጃ ማሕበር ውጤቶች አፈጻጸም አጠቃላይ ግምገማ ላይ አዲስ ከፍተኛ ደረጃ ስብሰባ ለ2025 ታቅዷል። በዚህ ታላቅ ስብሰባ ላይም የእድገት ሂደቶችን ለመገምገም እና ሁለቱንም ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች እና ተግዳሮቶችን ለመለየት እንደታሰበ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚያ በፊት ግን ኢትዮጵያ የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባኤን በመጪው ዓመት ህዳር ወር ላይ ታስተናግዳለች።

**ብሄራዊ የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባኤ**

የኢትዮጵያ መንግሥት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም የፈጠራ ዘርፍ ልዩ ትኩረት መስጠቱን የሚያመለክቱ በርካታ ተግባራትን እያስተዋልን እንገኛለን። ከዚህ ውስጥ ወጣቶች ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበት ማእከላትን መገንባትና ትላልቅ አገራዊ ፕሮጀክቶችን (እንደ ኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የመሰሉ) ይፋ ማድረግ ይገኝበታል። በቅርብ ጊዜ ወስጥ ደግሞ ዓለም አቀፍ ተሳትፎውን በማስፋት በዲጂታል ቴክኖሎጂ ምህዳር ውስጥ ለመግባት ልዩ ጥረት እየተደረገ መሆኑን የሚያመለክቱ ጉዳዮችን እያስተዋልን ነው። ለዚህ ማሳያው ከኢንተርኔት አስተዳደር የሚመለከተው ይገኝበታል።

በቅርቡም ኢትዮጵያ የመጀመሪያው ብሔራዊ የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ በአካል እና በኦንላይን ጥምረት አካሂዳለች። ጉባኤው በመጪው ዓመት ህዳር ወር በአዲስ አበባ የሚካሄደው የ 17ኛው ዓለም አቀፍ የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ(ፎረም) አካል እንደሆነ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ይፋ አድርጓል። በጉባኤው የበይነ መረብ ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ጥቅሞች፣ ተመጣጣኝ እና ትርጉም ያለው የበይነመረብ ተደራሽነት፣ እንደ መሰረታዊ መብት በሚሉት ጉዳዮች ላይ በትኩረት ተመክሮባቸዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ሁሪያ አሊ ከበይነ መረብ ጋር ተያይዞ የሚመጡ አሉታዊ ጫናዎችን ለመቋቋምና ዜጎች በበይነ መረብ የሚያደርጉት ግኑኝነት አስተማማኝ እንዲሆን የሚያስችሉ ልዩ ልዩ አዋጆች በስራ ላይ እንዲውሉ መደረጉን ይናገራሉ።

> **ከሶስት ወራት በኋላ የሚካሄደው 17ኛውን ዓለም አቀፉ የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባኤ ስኬታማ ለማድረግ፣ የሚነሱ ውይይቶች ሁሉን አቀፍ፣ ከዓለም አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተናበቡና የሚነሱ ሃሳቦች በነጻነት የሚንሸራሸሩበት መድረክ እንዲሆን የኢትዮጵያ መንግሥት ቁርጠኛ መሆኑን አረጋግጠዋል።**

ከሶስት ወራት በኋላ የሚካሄደው 17ኛውን ዓለም አቀፉ የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባኤ ስኬታማ ለማድረግ፣ የሚነሱ ውይይቶች ሁሉን አቀፍ፣ ከዓለም አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተናበቡና የሚነሱ ሃሳቦች በነጻነት የሚንሸራሸሩበት መድረክ እንዲሆን የኢትዮጵያ መንግሥት ቁርጠኛ መሆኑን አረጋግጠዋል።

የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ባልቻ ሬባ በይነ መረብ ከጥቅሙ ባሻገር ከመረጃ መረብ ወንጀሎች፣ ከጥላቻ ንግግሮች፣ የሀሰትና የተዛቡ ዜናዎች ስርጭት አኳያ የተለያዩ ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አሉታዊ ጎኖች እንዳሉት ያስረዳሉ። በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገውም ሆነ በህዳር ወር በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄደው ጉባኤ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የመፍትሄ ሃሳቦች የሚንሸራሸሩበት መሆኑን ጠቁመዋል። በተለይ በአገር አቀፍ ደረጃ የተሰናዳው ጉባኤው ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ለምታስተናግደው 17ኛው ዓለም አቀፍ የበይነ ምረብ አስተዳደር ጉባኤ መሰረት የሚጥል ነው ተብሏል። ገጽታ ለመገንባት፣ ኢትዮጵያ በመስኩ እየሰራች ያለውን ስራ ለዓለም ለማሳየት፣ የኢትዮጵያን ብሎም የአፍሪካን ተሰሚነት ለማሳደግ፣ ከተለያዩ ዓለምአቀፍ ተቋማት ጋር ትስስር ለመፍጠር እንዲሁም ለውጭ ምንዛሬ ግኝት ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። የበይነ መረብ አስተዳደር ፎረም አስገዳጅ የሆኑ ውሳኔዎች የሚወሰኑበት ሳይሆን ውሳኔ አመንጪና ሰጪ የሆኑት የግሉ ዘርፍና መንግሥት በጉዳዮቹ ላይ መክረው የመረጃና የፖሊሲ ሀሳብ መነሻ ሆኖ የሚያገለግል ነው።

**ጥቂት እውነታዎች**

17ኛው የዓለም አቀፍ የበይነ መረብ አስተዳደር ዝግጅት ሂደትን አስመልክቶ በብሄራዊ አስተባባሪ ኮሚቴው የኢትዮጵያ መንግሥት አቋቁሞ ስራ ጀምሯል። ይህ ኮሚቴ የተለያዩ ተግባራትን ሲያካሂድ ቆይቷል። በተለይ ዓለም አቀፍ ጉባኤው ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ከመሆኑ አንፃር በስኬት እንዲጠናቀቅና ኢትዮጵያም ከዚህ መሰል ታላቅ ዝግጅት አትራፊ እንድትሆን በልዩ ትኩረት እየተሰራ መሆኑን መንግሥት በየደረጃው ይፋ እያደረገ ነው።

የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ አማካይነት ኢ.ኤ.አ በ 2006 ዓ.ም ይፋ ከተደረገ ጀምሮ ሲካሄድ የነበረ ጉባኤ ነው። ኢትዮጵያም 17ኛውን የኢንተርነት አስተዳደር ጉባኤ ኢ.ኤ.አ 2022 እንድታስተናግድ ተመርጣለች። ይህንን ተከትሎ ነው መንግሥት ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን እያደረገ ነው የሚገኘው።

የኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስትር መረጃ እንደሚያመለክተው ጉባኤው ከበይነ መረብ እድገት ጋር የተያያዙ አንገቢጋቢ ጉዳዮችን፤ በይነ መረብ አስተዳደርና ሌሎች በበይነ መረብ በድጂታል ቴክኖሎጂዎች ጋር የተገናኙ ጉዳዮች ላይ ከተለያዩ የዓለም ክፍል የሚመጡ የግሉ ዘርፍ፤ መንግሥትና የዘርፉ ፖሊሲ አውጪዎች በተገኙበት የሚካሄድ እና በበይነ መረብ አስተዳደር ላይ የሚነሱ ሃሳቦች የጋራ ግንዛቤ የሚፈጠርበት መድረክ ነው። የዲጂታል ቴክኖሎጂ እና የበይነ መረብ አስተዳደርን በተመለከተ በየዓመቱ በሚካሄደው መሰል ፎረም ላይ ከተለያዩ ሀገር የተውጣጡ ተወካዮች ተገናኝተው የሚወያዩበት፤ መረጃ የሚለዋወጡበት፤ ልምድ የሚቀስሙበት እንደሆነም ይሄው መረጃ ያሳያል።

የኢንተርኔት አስተዳደር ፎረሙ ከኢንቴርኔት ጋር ተያይዞ ያሉ ዕድሎችን እንዲሁም ፈተናዎችና ተግዳሮቶችን በተመለከተ የሚነሱ ሃሳቦች የሚንሸራሸርበትና የጋራ ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው።

ኢትዮጵያ የምታሰናዳውን የጉባኤውን ዝግጅት አስመልክቶ መሰናዶውን ስኬታማ የሚያደርጉ ውይይቶች እየተደረጉ ይገኛሉ። አጠቃላይ ዝግጅቱም ከውጭ ጉዳይ፤ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ፤ ኢትዮጵያ አየር መንገድ፤ ጉሙሩክ ኮሚሽን፤ ከገቢዎች ሚኒስቴር፣ ገንዘብ ሚኒስቴር፤ ፌዴራል ፖሊስ፤ ኢትዮ ቴሌኮም፤ ጤና ሚኒስቴር፣ ከቱሪዝም ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን፣ ከብሄራዊ ባንክ በቅንጅት የሚሳተፉበት ነው።

**እንደ መውጫ**

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን ቀርፃ እና አጽድቃ ወደ ስራ ገብታለች። ከዚህ የስትራቴጂ ሰነድ እንደምንረዳው ዲጂታል ኢትዮጵያ የዲጂታል እድሎችን በመጠቀም ፈጠራ የታከለበትና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል በኢትዮጵያ መንግሥት የሚመራ ተነሳሽነት መሆኑን ነው። ከአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ እና የአስር ዓመት የልማት ዕቅድን ከመሳሰሉ ቁልፍ አገራዊ ስትራቴጂዎች ጋር እንዲሁም እንደ አፍሪካ ህብረት አህጉራዊ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ካሉ ዓለም አቀፍ ስትራቴጂዎች ጋር የተሳሰረ መሆኑንም ያስረዳናል።

ይህን ስትራቴጂ ለማሳካት ደግሞ በመጪው ህዳር ወር የሚካሄደው "ዓለም አቀፍ የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ" አይነት መድረኮች ጠቀሜታቸው የጎላ ነው። በተለይ የበይነ መረብ አጠቃቀም ፍትሃዊነት፣ እድገትና አስተዳደርን በተመለከተ ኢትዮጵያ ከአደጉ አገራት ልምድ ለመለዋወጥ እድሉን በስፋት የምታገኝበት ይሆናል። ከዚያም ባለፈ የአገር ገጽታን ለመገንባት፣ ወጣቶች በዲጂታል ቴክኖሎጂና መሰል ዘርፎች ላይ በቀጥታ ተሳታፊ እንዲሆኑና ትስስር እንዲፈጥሩ አጋጣሚውን የሚከፍት ዝግጅት እንደሚሆን የጠበቃል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የሕወሓት መገለጫ ባህሪ

አስመረት ብስራት



አቶ ሲሳይ ሃይለማሪያም



አቶ ሙሉብርሃን ሃይሌ

ሕወሓት ገና ከምስረታው ጀምሮ የሚታወቅበት አንዱ መገለጫው ዘረፋ ነው። ከተመሰረተበት ካለፉት 50 ዓመታት ጀምሮ ለትግራይ ሕዝብ ነጻነት ቆሜያለሁ ቢልም በተግባር ግን ለተቸገረውና ለተራበው የትግራይ ሕዝብ በተለያየ ጊዜ የመጣን እርዳታ ሲዘርፍ እና ሲሸጥ ቆይቷል። በቅርቡም ይህንኑ የዘረፋ ተግባሩን በጠራራ ጸሀይ ፈጽሟል ሲል የዓለም ምግብ ፕሮግራም አስታውቋል።

የዓለም ምግብ ፕሮግራም እንዳስታወቀው፤ ሕወሓት የዓለም ምግብ ፕሮግራም መጋዘን ውስጥ የነበረ ከግማሽ ሚሊዮን ሊትር በላይ ነዳጅ ዘርፏል። የዘረፈውንም ነዳጅ በአፋጣኝ እንዲመልስ አሳስቧል። በነዳጁ መዘረፍ ምክንያት የሰብዓዊ እርዳታዎች ለማሳለጥ መቸገሩን ገልጿል። እንዲሁም ቡድኑ የፈጸመው እጅግ አስነዋሪ ተግባር መሆኑን ሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጭምር ያወገዙት ሲሆን ከእነዚህም መካከል የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቃል አቀባይ ስቴፈን ዱጃሪክ እና በኢትዮጵያ የሩሲያ አምባሳደር ኢቭጌኒ ተረኪሂን ይገኙበታል።

በኢትዮጵያ የሩሲያ አምባሳደር ኢቭጌኒ ተረኪሂን ፤ ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት እንዳሉት ፤ በመጋዘኑ ውስጥ የነበረው የምግብና የነዳጅ ክምችት በአስቸጋሪ ሁኔታ ለነበሩ ዜጎች ሰብዓዊ ድጋፍ የሚውል ነበር። በሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ችግር ሰለባ ለሆኑ የትግራይ ማሕበረሰብ መድረስ የነበረበት እርዳታ በሽብር ቡድኑ መዘረፉ ተቀባይነት የሌለውና አስነዋሪ ተግባር ነው ማለታቸው ይታወሳል። ዘራፊዎቹ ነውረኛ ድርጊታቸውን ከደው ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የትግራይ ሕዝብ ለችግር ተዳርጓል የሚል የተለመደ ልፋታቸውን እንደሚቀጥሉና የሕዝብ ተቆርቋሪ ለመምሰል እንደሚሞክሩም ነው የገለጹት።

ከዚህ ቀደምም ሕወሓት በወረራ በቆየባቸው የአፋርና የአማራ ክልሎች ለተረጂዎች የተላከን ምግብ፣ መድሃኒት እንዲሁም የሕጻናት አልሚ ምግብ በመዝረፍ ለወታደራዊ አገልግሎት እንዲውል ማድረጉ ይታወሳል። በነሃሴ ወር 2014 ዓ.ም ወያኔ የዩኤ ስ ኤ አይዲ (USAID) መደብሮች ውስጥ በመግባት የእርዳታ የምግብ እህል ዘርፏል። የእርዳታ ምግብ ጭነው ወደ ትግራይ የገቡ ከ 100 በላይ የጭነት መኪናዎችን ከነጫኑት ቁሳቁስ ዘርፏል።

ይሄ ተደጋጋሚ የሕወሃት የዘረፋ ድርጊት እንደምታ ምንድነው? የቡድኑን ባህሪ ቁልጭ አድርጎ ለያሳይም ስንል የጠየቅናቸው የሕወሓትን ባህሪ ከመሰረቱ የሚያውቁትን የቀድሞ የሕወሓት ታጋይ አቶ ሲሳይ ሃይለማሪያምንና የትግራይ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ትዴፓ) የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሃን ሃይሌ ናቸው።

አቶ ሲሳይ እንደሚሉት ፤ ሕወሓት ሲፈጥረው የሰው ሀብትና ንብረትን ለመቀማት የተፈጠረ የአንድ ቤተሰብ ስብስብ ድርጅት ነው። ይህ ሲባል ሕወሓት ከዓድዋ አካባቢ የመጡ የአንድ ቤተሰብ ስብስብ ቡድን ነው። በዝምድናና በዘር ግንድ የተሳሰረ በአካባቢ ልጅነት የተዋቀረ ቡድን ነው።

ለመዝረፍ ሲፈልጉ ተቀናጅተው ነው ። ለአብነት በ1977 ዓ.ም ለእርዳታ የመጣውን እህል ከተራበው የትግራይ ሕዝብ ጉሮሮ ነጥቀው ለሠራዊታቸው ቀለብ አውለውት እንደነበር ዓለም የሚያውቀው ሃቅ ነው። በሌላ በኩልም በ 1984 ዓ.ም የወልቃይትን መሬት ለመዝረፍ ሲያቅዱ ከአራት መቶ ሺ በላይ ነዋሪዎች አፈናቅሎ የራሴ የሚላቸውን ሲያሰፍር እንደነበር ያስታውሳሉ። በሃያ ሰባት ዓመት የሥልጣን ዘመናቸው ሀገርና ሕዝብን ሲዘርፉ እንደነበር ይናገራሉ። እዛው ትግራይ እንደርታ ውስጥ ወደ ሶስት መቶ ሃምሳ ሺ ሰው አምጥተው አስፍረው የነበረ ሲሆን አንድ የዓድዋ ተወላጅ የሆነ የእነሱ ቤተሰብ ሁመራ ቦታ አለው፤ ወልቃይት፤ ሽሬ፤ እንደርታና ራያ ላይ ቦታ አለው። አንድ ሰው ቢያንስ አምስት ስድስት ቦታ ይዞ ከመሬት እስከ ንብረት ሲዘርፉ መኖራቸው የቀደመ ማንነታቸውም ከዘረፋ ጋር የተቃኘ መሆኑን እንደሚያሳይም ነው የሚያብራሩት።

ይሄ ቡድን ባህሪው ዘረፋ ነው፤ የሌብነት ነው። 27 ዓመት በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜም ይህንኑ ሲያደርግ ቆይቷል፤ ኩራዝ ስኳር ፋብሪካ ለመመስረት የታቀደው እነ ስብሃት ነጋ፤ እነ አባ ፀሀየ በአጠቃላይ የሕወሃት ቤተሰብ አዲስ አበባ ከተማ ተቀምጠው ቦታ ተመርተው ፋብሪካው ሊመሰረት ሲል በባለቤትነት ብዙ ገንዘብ ስለመቀበላቸው ይገልጻሉ።

ሕወሓት የደም ድርጅት ነው። በሰው ላብ በሰው ደም መክበር ይፈልጋል። አሁን እራሱ እስከ ሰሜን ሸዋ ድረስ መጥተው ዘርፈዋል። በዘረፉት ገንዘብም መቀሌ ላይ የተለያዩ አይነት ሱቆች መክፈታቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ መሆኑን ያብራራሉ።

አሁን ላይ መንግሥት ለተቸገረው ለስድስት ሚሊዮን የትግራይ ሕዝብ የሚሆን እርዳታ አስገብቷል፤ ይህ የእርዳታ እህል በሕወሓት መጋዘን ተቆልፎበት ነቀዝ እየበላው ይገኛል። ሕወሓት ከድሀ ሕዝብ ጉሮሮ ላይ የሚነጥቅ ድርጅት መሆኑ ሳያንሰው አሁን ደግሞ ከሕዝብና ከመንግሥት አልፎ የዓለም አቀፍ እርዳታ ድርጅቶችን ንብረት መዝረፍ መጀመሩ ምን አይነት የሞራል ዝቅጠት ላይ እንዳለ ማሳያ ነው ሲሉ ይናገራሉ።

እንደ አቶ ሲሳይ ገለጻ፤ መቀሌ ውስጥ ነዳጅ ጠፋ በማለት ያላቸውን ለሕዝብ የሚያካፍሉ የትግራይ ሕዝብ አሳቢ መስለው ለመታየት ይሞክራሉ። በተግባር ግን ነዳጅም ሆነ ሌሎች የእርዳታ ቁሳቁሶች ሕዝቡ ጋር ሳይሆን እየወሰዱ ያሉት ለእነሱና ላሰለፉት ሃይል ነው ። የትግራይ ሕዝብ በመድሃኒትና በምግብ እጦት እየሞተ ነው። ከ2010 ዓ.ም እስካሁን ድረስ የትግራይ ሕፃናት ክትባት አላገኙም ። ነገር ግን ይህ በሕዝብ ስም መነገድ ነው። ይሄም የሚታወቅ የኖረበት ባህሪው ነው። አሁንም ለሕዝቡ የመጣውን መድሃኒት በሕገ ወጥ መንገድ መድሃኒት መደብሮችን በመክፈት ለሕዝቡ በውድ ዋጋ እየሸጠ መሆኑ በማስረጃ አረጋግጠናል።

ሕወሓት የትግራይ ሕዝብን እንደ ሕዝቡ አያየውም። ቢያየው ኖሮ ሕፃናትን ለጦርነት እየማገደ ትውልድ አይሰርቅም ነበር። ሌብነቱ ሕዝብን፤ ወጣቶችን፤ የሰውን እድሜ ሳይቀር እየሰረቀ መሆኑን አብራርተዋል። አርባ ሃምሳ የማይሞሉ ወሮበሎች የትግራይ ወጣቶችን ሕይወት ለሥልጣን ጥማታቸው ማርኪያ ሲሉ እየሰረቁ መሆኑ አሳፋሪ ተግባር ነው ይላሉ አቶ ሲሳይ ።

አቶ ሲሳይም በዚህ ሃሳብ በመስማማት በአሁኑ ሰአት የትግራይ ሕዝብ የሕወሓት አመራር አንገሽግሾታል። በየቀኑ ተቃውሞ በማድረጉ በየቀኑ እየተገደለ መሆኑ ይታወቃል፤ ሕዝባችንን እንደ ኢትዮጵያዊ የምናየው ከሆነ ልናግዘውና ነፃ እንዲወጣ ይገባል ይላሉ። የዚህ ሁሉ ችግር መፍትሄው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይህንን ሃይል ማጥፋት ነው የሚሉት አቶ ሲሳይ በመላው ሀገሪቱ ያለውን አለመረጋጋትና ጦርነት ለማስቀረት የግድ መጥፋት ይኖርበታል። የትግራይ ሕዝብም ስብሰባ ሲጠራ ባለመሄድ፤ ልጆቹን በመጠየቅ እየታገለ ይገኛል።

የትግራይ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ትዴፓ) የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሃን ሃይሌ በበኩላቸ፤ የሕወሓት አመራር ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ የዝርፊያ ወንጀሎችን እየሰራ የመጣ ቡድን መሆኑን ይናገራሉ። ቀደም ሲል ለ17 ዓመታት በተደረገው የትግል ወቅት ጭምር በተራበው የትግራይ ሕዝብ ስም የመጣ የእርዳታ እህል እየሰረቀ እና እየሸጠ ለግል ጥቅሙ ሲያውል መቆየቱንም ያስታውሳሉ።

**አሁን ላይ መንግሥት ለተቸገረው ለስድስት ሚሊዮን የትግራይ ሕዝብ የሚሆን እርዳታ አስገብቷል፤ ይህ የእርዳታ እህል በሕወሓት መጋዘን ተቆልፎበት ነቀዝ እየበላው ይገኛል። ሕወሓት ከድሀ ሕዝብ ጉሮሮ ላይ የሚነጥቅ ድርጅት መሆኑ ሳያንሰው አሁን ደግሞ ከሕዝብና ከመንግሥት አልፎ የዓለም አቀፍ እርዳታ ድርጅቶችን ንብረት መዝረፍ መጀመሩ ምን አይነት የሞራል ዝቅጠት ላይ እንዳለ ማሳያ ነው**

በሥልጣን ላይ በነበሩ ጊዜ ደግሞ የትግራይ ሕዝብ በሴፍትኔት፣ በእርዳታ ምግብ በሚኖር ወቅት በርካታ ሕዝብ እየተቸገረ እያለ እንኳን ለካድሬዎችና ደጋፊዎቹ የተዘረፈ ሀብት እንዲያካብቱ ሲያደርግ መቆየቱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ መሆኑን ያስታውሳሉ።

አሁን ደግሞ ሕዝቡን በጦርነት ሰቆቃ ውስጥ መክተቱ ሳያንስ ለዚህ ሕዝብ በእርዳታ የሚገባ መድሃኒት ለራሱ ካድሬዎች እንዲጠቀሙበት ፣ አዳዲስ መድሃኒት ቤቶችን በመክፈት እየሸጠ መሆኑን ይናገራሉ። ይህ የትግራይ ሕዝብ ጠላት የሆነው ሕወሓት ጦርነቱን በጀመረ ዋዜማ በረሃብ ምክንያት በሞት አፋፍ ላይ ያሉትን የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር ለመድረስ ከዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ የተሰበሰበውን ከ 570ሺ ሊትር በላይ ነዳጅ ከሚያጣጥሩት ረሃብተኛ ወገኖች አፍ መንጠቁ ከፍተኛ ውግዘት አድርሶበታል ይላሉ።

ይህ ሁሉ በሥልጣንም ላይ እያለና ከሥልጣን ከወረደም በኋላ እያደረጋቸው ያሉት ተግባር የቡድኑን የዝርፊያ ታሪክ እንዲሁም ነጥቆ መብላት ባህሪው እንደሆነና አብሮት አድጎ አብሮት ያረጀ እኩይ ተግባሩ ስለመሆኑ ለመረዳት አያስቸግርም ። ሕወሓት አሁንም ከ 500ሺ በላይ ወጣቶችን ጨርሶ፤ የቀረው ተዳክሞ ተስዶ ባለበት ሁኔታ፤ ሕዝቡ በረሃብ፣ በመድሃኒት እጦት ለማለቃቸው ምክንያት መሆኑ የማያሳስበው እኩይ ቡድን መሆኑን ይናገራሉ።

የትግራይ ሕዝብ ችግር በሕወሓት የማይፈታ መሆኑን ሕዝቡ ማመን እንዳለበት የሚናገሩት አቶ ሙሉብርሃን ይህንን እምነት ይዞ ለውጥ ሊያመጣ ይህንን ሃይል ለማስወገድ የሚችል የሚመጥን ትግል ሊደረግ እንደሚገባም ነው የሚናገሩት ።

ሕወሓት የትግራይን ሕዝብ አሁንም በከፍተኛ ሁኔታ በማስገደድ ወደ ጦር ግንባር እንዲዘምት፣ እንዲዋጋ ለማድረግ በሚተጋበት ጊዜ መንግሥት ግን ለሕዝቡ የተገኘውን ያህል ሰላም በመመኘት ያለ ቅድመ ሁኔታ ለመደራደር እንደሚፈልግ የሰጠውን የሰላም አማራጭ በመመልከት ሕዝቡ በቃኝ ሊለው ይገባልም ባይ ናቸው።

የትግራይ ሕዝብ ለሰላሙና ለአንድነቱ ሲል ይሄንን ቡድን ከላዩ ላይ መንግሎ መጣል አማራጭ የሌለው ምርጫ መሆኑን ይጠቅሳሉ። የሀገሪቱ መንግሥትም ሆነ የሕወሓት ተቃዋሚ ሃይሎች የበኩላቸውን ጥረት እያደረጉ ቢሆንም ትልቅ ግፊት ግን ከሕዝቡ ሊነሳ ይገባል ይላሉ።

እርግጥ ነው በርካታ አካባቢዎች ተቃውሞዎች አመፆች መኖራቸውን አይካድም ያሉት አቶ ሙሉብርሃን ሕዝቡ ይሄንን ለሀገርም ለወገንም የማይጠቅም ሃይል በቃኝ ብሎ ከራሱ ማውረድ ይኖርበታል። የትግራይ ወጣት ወንጀለኞችን ሕዝብ ውስጥ ለመደበቅ ሲባል በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች መስዋእት መሆን እንደሌለባቸው ተረድቶም አፈሙዙን ወደ ሕወሓት ማዞር አማራጭ መሆኑን አስረድተዋል።

ሁለቱም ፖለቲከኞች እንደሚስማሙበት ፤ የሕወሓት ዋነኛ መገለጫ ባህሪው ዝርፊያ ነው። ከትግል ወቅት ጀምሮ በሥልጣን ላይ እያለም ይሄው ባህሪው በተለያየ መልኩ ታይቷል። አሁንም ከሥልጣን ቢባረርም ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳሉ እንዲሉ ለተረጂዎች የመጣን ሰብአዊ እርዳታ ፣ መድሃኒትና የእርዳታ ማጓጓዣ ነዳጅ ጭምር ሲዘርፍ ታይቷል። በአጠቃላይ ይሄ ቡድን ለትግራይ ሕዝብ የቆመ ሳይሆን በትግራይ ሕዝብ ቁስል ላይ ጨው እየነሰነሰ የትግራይን ሕዝብ ለስጋይ ለሰላም እጦት የሚዳርግ ነው። ዝርፊያውም በታሪክ የሚታወቅበት መገለጫው ነው።

ማህበራዊ

# ሴቶች

## ሙያና ጊዜያቸውን ለመልካም ሥራዎች ያዋሉት በጎዋ ሴት

**ሰላማዊት ውቤ**

መምህርት አሚና መሐመድ የሱፍ ሀገራቸውን በብርቱ ይወዳሉ። ዜጎችን ማገልገል ያረካቸዋል። የትኛውም የሰው ልጅ እንዲራብ፤ እንዲታረዝና እንዲጠማ አይሹም። በየትኛውም ሁኔታ ሲበደል፤ ሲገፋና ሲቸገር ማይት አይሆንላቸውም። ዛሬም በጡረታ ጊዜያቸው ማልደው ከቤታቸው በመውጣት ማታ ላይ የሚመለሱት እንባ አብሰው ረክተው ደስ ብሏቸው ነው። በዚህ መልኩ ሁለት ሶስት ሰው ነጻ ሳያደርጉ ወደ ቤታቸው ገብተው አያውቁም። በተለይ በባህልና በኢኮኖሚም ሆነ ሕብረተሰቡ ለሴቶች ባለው የተዛባ አመለካከት እየተጎዱ የመጡ ሴቶችንና የሀገርን ችግር ቢችሉ ከኪሳቸው ባይችሉ ሕብረተሰቡን በማስተባበር መቅረፍ የተለመደ ተግባራቸው ነው። ሕወሓት ከአንድም ሁለቴ በከፈተው ጦርነት ለተጎዱና ለተፈናቀሉ ወገኖች እንዲሁም ለጀግናው መከላከያ ሠራዊት በግላቸው በገንዘብና በጉልበታቸው እንዲሁም ሕብረተሰቡን በማስተባበር ድጋፍ በማድረጉ ረገድ ቀዳሚ ናቸው። ወደ ሦስት ሚሊዮን የሚጠጋ የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ አሰባስበው ሰጥተዋል። በሶ፤ ቋንጣ፤ ድርቆሽ ፤ማኮሮኒ፤ ፓስታና የተለያዩ አልባሳት በእሳቸው አስተባባሪነት ከተደረገው ድጋፍ ይጠቀሳሉ። አሁንም ቡድኑ ለሦስተኛ ጊዜ ባደረገው ወረራ በዚሁ መልኩ ያሰባሰቡትን ዱቄት፤ ሩዝ፤ ፓስታ፤ ማኮሮኒና የተለያዩ አልባሳት ሰብሳቢ በሆኑበት በድሬዳዋ ሴቶች ማህበር ቢሮ ውስጥ በማኖር ለመከላከያ ሠራዊቱና በጦርነቱ አካባቢ ላሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ለማድረስ በዝግጅት ላይ ይገኛሉ።

ይሄንኑ ድጋፍ ችግሩ እስከሚፈታ አጠናክሮ ለማስቀጠልም በትጋት ደፋ ቀና እያሉ ነው።

በድሬዳዋ ምድር እኝህን በጎ ሴት የማያውቅ የማሕበረሰብ ክፍል የለም። ማሕበረሰቡ በሁለት ጉዳዮች አብዝቶ ያውቃቸዋል። አንደኛው ለ36 ዓመታት ባገለገሉበት በመምህርነታቸው ሲሆን ሁለተኛው በበጎነታቸው ነው። በዚሁ በበጎነታቸው ከልጆቻቸው አልፎ በድፍን ድሬዳዋ ነዋሪዎች ማዘር ትሬዛ የሚል ቅጽል ስምም ተሰጥቷቸዋል። አሁን ላይ የድሬዳዋ ከተማ ከንቲባ የሆኑትን ጨምሮ በርካታ ኃላፊነት ላይ ያሉ ተማሪዎችን ያፈሩበትን 36ቱን ዓመታት የመምህርነት ሙያቸውን ያሳለፉትም የቀለም ትምህርቱን ከማስተማር ባሻገር በነዚህ ዙሪያ አያሌ በጎ ተግባራቶችን በማከናወንም ነው። ከድሬዳዋ ከተማ ከ30 እስከ 40 ኪሎ ሜትር በሚርቅ የገጠር ክፍል የሚኖሩ በርካታ ልጃገረዶችን የኢኮኖሚ ችግር በግላቸውና በጋራ ድጋፍ በመቅረፍ ወደ ድሬዳዋ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንዲመጡ ያደረጉበት የድሬዳዋ የገጠር ሴት ተማሪዎች መኖርያ አንዱ ማሳያ ነው።

በድሬዳዋ ከተማም ሆነ በአጠቃላይ በሀገራችን የመጀመሪያው በሆነው በዚህ የሴቶች ሆስቴል 38 የገጠር ገበሬ ማህበራት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ልጃገረዶችን የሁለተኛና የከፍተኛ ትምህርት ተቋዳሽ አድርገዋል። ዛሬም በጡረታ ከተገለሉ በኋላ የመሰረቱትን ሆስቴል በዳይሬክተርነት እያገለገሉ የሚገኙት መምህርት አሚና ዛሬ ብዙዎቹ በተለያዩ የሥራ መስኮች በመሰማራት ከራሳቸው አልፈው ቤተሰባቸውን ብሎም አገራቸውን በተለያየ መንገድ መጥቀም የሚችሉ እንደሆኑላቸው ይናገራሉ። ሁሉም በሥራ የመሰማራታቸው ምስጢር ድሬዳዋ ላይ ከሆስቴል የወጡ ተማሪዎች በተገኘው ሥራ ላይ እንዲመደቡ ካቢኔው መወሰኑንም ያወሳሉ። በክራንችና በዊልቸር የሚሄዱትን ጨምሮ በርካታ አካል ጉዳተኛ ሴቶች የዕድሉ ተጠቃሚ መሆናቸውንም ያነሳሉ። የተወሰኑትም ከዲግሪ በላይ በትምህርት ለመግፋት ወደ ውጭ ወጥተዋል። ባህላችን ዲግሪያችን ነው። በኋላ ላይ ዲግሪው የሚያመጣውን ባል እንጠብቃለን የሚል የአስተሳሰብ ለውጥ አምጥተዋል። በለውጡም ለ 38ቱ ገጠር ቀበሌ ማሕበረሰብ አርአያ መሆን ችለዋል። ዘንድሮም 12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ለመውሰድ በዝግጅት ላይ ካሉ በርካታ ሴት ተማሪዎች መካከል



በጎ አድራጊዋ መምህርት አሚና መሐመድ

በተፈጥሮ ሁለት እጅ የሌላትና የማትናገር ተማሪዎች በሆስቴሉ እንደሚገኙ ይገልፃሉ።

ሆስቴሉ ባይኖር አካል ጉዳተኞችን በሴትነት ከሚደርስ ተደራቢ ችግር ጋር እዚህ ደረጃ ላይ ማድረስ ይቻል እንዳልነበረ የሚያወሱት መምህርቷ የዛሬ 14 ዓመት ሆስቴሉ ወደ ስራ ሲገባ የነበሩትን ተደራራቢ ፈታኝ ችግሮችም ሆስቴሉን ለመመስረት ካነሳቸው ምክንያት ጋር እያዋዙ አጫውተውናል።

እንዳወጉን ለመመስረት ያነሳሳቸው ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ዘጠኝ የከተማና 38 የገጠር ቀበሌ ገበሬ ማሕበር አላት። 38ቱ ቀበሌዎች ከድሬዳዋ ከተማ በትንሹ ከ30 እስከ 40 ኪሎ ሜትር ይርቃል። ከ14 ዓመት በፊት ታዲያ ከነዚህ ቀበሌዎች መጥቶ ድሬዳዋ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ከፍተኛ ትምህርት ተቋም መጥቶ የሚማር ሴት ተማሪ አልነበረም። ምክንያቱ ፈርጀ ብዙ ቢሆንም ገዢው የአካባቢው ማሕበረሰብ ሴት ተምራ የት ትደርሳለች የሚል ለሴት ልጆች የነበረው የተዛባ አመለካከት ነበር። ከዚህ ተነስቶ ትምህርት ቤት የሚልከው ወንድ ልጆቹን ነበር።

አሚና ከመምህርነት ወደ ትምህርት ቢሮ ተዛውረው አቅም ግንባታ ላይ መምጣታቸው ምክንያቱን እንዲመረምሩ አገዛቸው ። በአራት ከላስተር የተደራጀውን 38 የገጠር ቀበሌ ገበሬ ማሕበር ነዋሪ ማሕበረሰብን አወያዩ ። የኢኮኖሚ ችግር ስላለብን ሴት ልጆቻችንን ወደ ድሬዳዋ አምጥተን ማስተማር አንችልም። ማስተማር የምንችለው እስከ አራተኛ ክፍል ነው። ግፋ ቢልም ስድስተኛ እና ስምንተኛ ክፍልን ነው የሚል ምላሽ ሰጧቸው። ከዚህ በኋላ ሴት ልጆቻቸውን መዳር እንደሚፈልጉም አቅጨን ነገሯቸው። ምክንያታቸው የሴቷ ማግባት የሚያስቀርላቸው የኢኮኖሚ ጫና እንዳለውም አስረዷቸው።

ሌላው ወደ ትምህርት ቤት የማይመጡበት ዋናው ችግር ሩቅ መሆኑና ቤት ተከራይቶ ማስተማር ያለመቻሉ ነበር፡፡ ድሬዳዋ ላይ በቅርበት የምትማሩበት ብታገኙስ ብለው ጠየቋቸው። ሁሉም በአንድ ቃል ልጆቻቸውን ልከው እንደሚስተምሩ ገለጹላቸው። ማረፊያ ያጡ አንዳንድ ሴት ልጆችን በግላቸው ማረፍያ እየሆኑ ያግዙ የነበሩት አሚና ጊዜ አላጠፉም ። ከውይይቱ መልስ በፍጥነት በቁጭት ሆስቴሉን የመገንባት ፕሮጀክት ቀርፀው ለመንግሥት አቀረቡ። ምንም ዓይነት ተቃውሞ ሳይገጥመው ፕሮጀክታቸው ፀደቀና በ1999 ዓ.ም ግንባታው ተጠናቀቀ።

ሆኖም ወቅቱ በበርካታ ፈተናዎች የታጠረ ነበር። ኮንትራክተሩ ቁልፉን ሲያስረክባቸውና ከስምንተኛ ክፍል ወደ ዘጠነኛ ክፍል ያለፉ 47 ሴት ተማሪዎች መግቢያ ካርዳቸውን ይዘው ወደሳቸው መጥተው ነበር። በተጨማሪም ድሬዳዋ በከባድ ጎርፍ አደጋ የተጎዳችበት ፤በወቅቱ የነበሩ የካቢኔ አባላት ተቀይረው በአዲስ የተተኩበት ነበር። እንዲሁም ሌሎች በርካታ ችግሮች የነበሩበት ሆነ ፤ እርሳቸውም ለጊዜው በግላቸው ለ47ቱ ተማሪዎች በእለቱ ማረፍያና ምግብ እየሰጡ ለዘላቂ መፍትሄ ልጃገረዶቹን እያስከተሉ መጮህ ጀመሩ። ‹‹ልመናና ማሕበረሰብ ማስተባበር ይዋጣልኛል›› የሚሉት በጎዋ ሴት ኦሮሚኛ፤ አማርኛና አደሪኛን ጨምሮ አረብኛ፤ እንግሊዝኛ ጨምሮ ከስድስት በላይ የሀገር ውስጥና የውጭ ቋንቋዎች በደንብ መናገር፤ ማንበብና መፃፍ በመቻላቸው ከተለያዩ ባለሀብቶች 600 የውሃ ቱቦዎች ድጋፍ አገኙ። በዚህ ሆስቴሉን ካፀዱ በኋላ ደግሞ መብራት አልነበረውምና እንዴት ከጭለማ ወጥተው ጨለማ ውስጥ በማደር ተምረው ውጤታማ ይሆናሉ በማለት ደግሞ ወደ መብራት ኃይል ሄደው ጮሁ። አቅማቸው ኩራዝ ከመግዛት የማያልፍና በኩራዝ ማጥናት ከተማ ውስጥ የማይታሰብ እንደሆነና መንግሥት ውሃ መብራት ያስገባል ብለው ወተወቱ። በዚህም ተሳክቶላቸው የመብራት ብርሃን አገኙ ። በሌላ በኩል ደግሞ ልጃገረዶቹን ወደ ማረፍያው አስገብቶ ለማኖር ከአንሶላና ፍራሽ ጀምሮ ምግብና መጠጥ እንዲሁም በርካታ ነገሮች ያስፈልጉ ነበርና የመምህርቷ እግር አሁንም ለልመና ከመሮጥ አልቦዘነም። ወደ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቢሮ አመሩ ከብዙ ውይይት በኋላ ልመና የሚሆንላቸው አሚና ኃላፊውን አሳምነው ማመልከቻ ጽፈው እንዲያስገቡ ተፈቀደላቸው። አስገብተውም አንሶላና ብርድ ልብስ፤ ፍራሽን ጨምሮ ሳህንና ሹካ ማኒኪያዎችና ብረት ድስት ተሰጣቸው። ይሄኔ በመኖርያ ቤታቸው፤ በሆቴሎችና በተለያዩ ቦታ ያሳረፏቸውን ልጃገረዶች ወደ ሆስቴሉ በማምጣት ማሳረፍ ቻሉ።

በጎዋ ሴት ልጃገረዶቹ በሆስቴሉ አርፈው ትምህርታቸውን መማር ከጀመሩ በኋላ በዩኒሴፍ የድሬዳዋ ፎካል ፐርሰን የነበሩትን ናይጀሪያዊት ሴት ሆስቴላቸውን እንዲጎበኙ አደረጉ ። በጉብኝቱም ሀስቴሉ ያለበትን ችግር ብሎም ለሴት ተማሪዎቹ የተመጣጠነ ምግብ ማቅረብ በትምህርታቸው ስኬታማ እንደሚያደርጋቸው ነገሯቸው። በዚህም ተወካዩ ከ 350 ሺ ብር በላይ እርዳታ አገኙ ። ልጃገረዶቹን እንደ ፍርኖ ዱቄት ፤ማኮሮኒ፤ ፓስታና ሌሎች ተመጣጣኝ ምግቦች እንዲመገቡ ማድረግ ተቻለ።

በዚሁ መልኩ ዩኒሴፍ ለ10 ዓመታት ያህል ሆስቴሉን ሲደግፍ ቆየ። በርካታ ውጤታማ ተማሪዎችም መውጣት ቻሉ። ከ10 ዓመት በኋላ ዩኒሴፍ ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም በማለት እዚህ ድረስ ካደረስናችሁ ራሳችሁን ቻሉ ሲል ደግሞ የክልሉ መንግሥት በጀት እንዲመድብለት አስደረጉ። ሆኖም በዓለማችን በተለይም ከተለያዩ ወቅታዊ ቀውሶች ጋር ተያይዞ በእጅጉ ካሻቀበው የምግብ ዋጋ ሊመጣጠን አልቻለም ። በተለይ በ2013 እና በ2014 ልጃገረዶቹ በእጅጉ የተራቡበት ነበር። ወደ ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ አቅንተው ፓስታ፤ ሩዝ፤ማኮሮኒና ዱቄት ለምነው በማምጣት በጀቱን ደጉመው ማለፍ ቻሉ። አንሶላና ብርድ ልብስ አላቂ እንደመሆናቸው በየጊዜው ለማሟላት የማያንኳኩት በር ብዙ ነው። አጋጣሚዎችን በመጠቀምም የሚወዳደራቸው የለም። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሴቶች ማሕበር ጥምረት ሥልጠና ለመስጠት በመጣበት ጊዜ አባላቱን ወደ ሆስቴሉ በማምጣት ልጃገረዶቹ ያሉበትን የኑሮ ሁኔታ በማሳየት እያንዳንዳቸው አዝነውና አልቅሰው ከአበላቸው ላይ አዋጥተው እንዳገዟቸውም ይናገራሉ ።

በጎዋ ሴት መምህርት አሚና እንዲህ እያሉ ነው ዛሬ ላይ ሆስቴሉን ያደረሱትና በርካታ ልጃገረዶች በትምህርትና በሥራቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ያስቻሉት።

አሁን ላይ ሆስቴሉ በጥሩ ሁኔታ ላይ ቢገኝም ኮምፒውተሮቻቸው አሮጌ በመሆናቸው በአዲስ ቢተኩና የኮምፒውተር ክፍሉ ቢጠናከር የሚል ሃሳብ አላቸው። ማጠናከሪያ (ቲቶር) ትምህርት የሚያገኙበት ሁኔታ በሆስቴሉ ውስጥ ቢመቻች ከሴቶች ንጽህና መጠበቂያ (ሞዴስ) ጀምሮ በተለያዩ ነገሮች ቢደገፉ እንዲሁም ተመጣጣኝ ምግብ ላይም ከኑሮ ውድነት አንፃር የመግዛት አቅሙ በመዳከሙ የክልሉ መንግሥት የሚመድበውን በጀት መደገፍ ያስፈልጋል የሚል እምነት አላቸው።

በጎዋ ሴት ተምሮ ሁለተኛ ዲግሪ እንዲይዝ ያደረጉትን የሆስቴሉን ጥበቃ ጨምሮ በርካታ ዜጎችን ከኪሳቸው እያወጡ ያስተማሩ፤ ሴት ተማሪዎች በሃይማኖትና በሥነምግባር እንዲታነፁ ደግሞ ከቤተሰብ የመጡና ብዙ የጠለቀ እውቀት ስለሌላቸው ተታለው ለአደጋ እንዳይጋለጡ ሰፊ ጊዜ ወስደው የሚያስተምሩ፤ ማሕበረሰቡ የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጣ ግንዛቤ የሚፈጥሩ ናቸው። በተለይ ከሼሪያ ፍርድ ቤት ጋር እና ከተለያዩ የሕግ አካላት ጋር በመሆን ባሎቻቸው ከቤት ያባረሯቸውን ሴቶች ወደ ቤት ይመልሳሉ። በጉልበትና በዕውቀት ማነስ ወይም በተዛባ ፍርድ የተቀሙትን ንብረት የሚያስመልሱ ናቸው። እኛም በቅርቡ ከስኬታማ ሴቶች አንዷ በመሆናቸው የታጬትንና ለብዙ የሙስሊም ሴቶች ጠበቃ በመሆን በባሎቻቸው የተቀማ ንብረት የሚያስመልሱ ከቤታቸው የተባረሩ ሴቶች ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ የሚያደርጉ ጠበቃ፤ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪና በጎ አድራጊ መምህርት ላይ ያተኮረ ጽሑፋችንን ደመደምን።

# ማረፊያ | አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

**የዛሬው የአዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን ከ54 ዓመት በፊት የታተሙ ጋዜጦች ይዘው የወጡትን ዘገባ ያስታውሰናል፡፡ ማኅበራዊ፣ ወንጀል ነክና እንስሳት ሕክምና ላይ ያተኮሩ ዘገባዎችን ለትውስታ ያህል መርጠናል፡፡ የደብረ ዘይት የከብት ሕክምና ኢንስቲትዩት የተለያዩ የእንስሳት በሽታ መከላከያ መድኃኒት እየቀመመ ለእንስሳት ሕክምና በሥራ ላይ ማዋሉ ከመረጥናቸው ዘገባዎች ተጠቃሽ ነው፡፡ ባለፈው እሁድ በዚሁ ጋዜጣ ላይ የወጡት ዶክተር ተስፋዬ ቢፍቱ ለበርካታ በሽታዎች (ከ100 በላይ) መድኃኒት ግኝት ባለቤት መሆናቸውን የሚያስታውሰንን ዘገባም ይዘናል፡፡**

## ለ፯ ሚሊዮን እንስሳት የሚበቃ መድኃኒት ተቀምሟል

ደብረ ዘይት፤ (ኢ.ዜ.አ.)፤ ደብረ ዘይት የሚገኘው የከብት ሕክምና ኢንስቲትዩት፤ በዚህ ዓመት ለ፯ ሚሊዮን ፬፻፵፫ሺህ ፭፻፺፭ እንስሳት የሚበቃ ልዩ ልዩ የእንስሶች በሽታ መከላከያ የሚሆን መድኃኒት መቀመሙን አንድ የኢንስቲትዩቱ ቃል አቀባይ ገለጠ፡፡

ቃል አቀባዩ ከዚህ አያይዞ እንዳስረዳው፤ የተቀመመው መድኃኒት ፭ ሚሊየን ፫፻፵፭ ሺህ ፪፻ ዶዝ ለቀንድ ከብቶች፣ ለአሳማዎች በሽታ መከላከያ መሆኑን ገልጧል፡፡

እንደዚሁም፤ በተለይ የተዘጋጀ ፓስቴውሪላ ፩፻፸፯ ሺህ ፩፻፳፭ ዶዝ፣ አባ ጎርባ ለተባለው በሽታ መከላከያ፤ ፩፻፸፩ ሺህ ፪፻፶ ዶዝ፣ ለአባ ሠንጋ በሽታ መከላከያ ፩ሺህ ዶዝ፣ ፋውል ታይፎይድ ማለት (የዶሮ በሽታ) ፭ሺህ ፭፻ ዶዝ፣ ፋውል ኮሌራ (የዶሮ) በሽታ መከላከያ የሆኑ መድኃኒቶችን ቀምሞ በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

ቃል አቀባዩ አቶ ጌታሁን አበጀ ከዚህም በማያያዝ፤ ኢንስቲትዩቱ ባለፉት አራት ዓመታት በርካታ መድኃኒቶችን ቀምሞ በየጠቅላይ ግዛቶቹ ታድለው በሥራ ላይ መዋላቸውን ከገለጡ በኋላ፤ የመከላከያ መድኃኒቱን ከውጭ አገር ስናስመጣ እዚሁ ስለሚቀመምና ስለሚዘጋጅ የከብት ሕክምና ዋና መምሪያ በሽታውን ለመከላከልም ሆነ፤ ፈጽሞ ለማስወገድ በየቦታው ያሠማራቸው ሠራተኞቹ መከላከያ መድኃኒት የማነስም ሆነ የማጣት ችግር አይገጥማቸውም፡፡

የመከላከያ መድኃኒቶቹን በላቦራቶሪ ውስጥ ቀምመው የሚያዘጋጁ አንድ ኢትዮጵያዊ ዶክተርና ሦስት የውጭ አገር ዶክተሮች ይገኛሉ፡፡ ከዚህም ሌላ በቂ ትምህርት ያላቸው ቴክኒሺያኖችና የዶክተሮቹ ረዳቶች መኖራቸውን ገልጠዋል፡፡

(ነሐሴ 11 ቀን 1960 ከወጣው አዲስ ዘመን)

## በሬ የሰረቀው ፩ ዓመት እሥራት ተቀጣ

አሰላ (ኢ.ዜ.አ)፤ በቀለ ቶልቻ የተባለው ሰው በተከሰሰበት የስርቆት ወንጀል በ፩ ዓመት እሥራት እንዲቀጣ የጭላሎ አውራጃ ፍርድ ቤት ግንቦት ፳፩ ቀን በዋለው ችሎት ፈረደ፡፡

ተከሳሹ ግንቦት ፲፪ ቀን የአቶ ጌታሁን ወልደማርያምን ሁለት በሬዎች ሰርቆ ሲነዳ ከነኤግዚቢቱ ተይዞ ተከስሶ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ፤ አድራጎቱን ራሱ ከማመኑም በላይ በሕግ ምስክሮች ተረጋግጦበታል፡፡ ስለዚህ ተከሳሹ በፈጸመው ወንጀል በ፩ ዓመት እሥራት እንዲቀጣ ሲበየንበት በእጁ የተገኙትም በሬዎች ለባለንብረቱ እንዲመለሱ ተወስኗል፡፡

በቀለ ቶልቻ ይህንን ወንጀል የፈጸመው፤ በአሩሲ ጠቅላይ ግዛት በጭላሎ አውራጃ በደራ ወረዳ መሆኑን ዐቃቤ ሕጉ አቶ ለገሠ መንግሥቱ ገለጡ፡፡

እንዲሁም በዚሁ አውራጃ ግዛት በኮፈሌ ወረዳ ሙዳ ሔይሳ የተባለ ሰው በፈጸመው የሥርቆት ወንጀል በ፩ ዓመት እስራት እንዲቀጣ የጭላሎ አውራጃ ፍርድ ቤት ግንቦት ፳፪ ቀን የፈረደበት መሆኑን ሕግ አስከባሪው በተጨማሪ ገለጡ፡፡

(ሐምሌ 10 ቀን 1960 ከወጣው አዲስ ዘመን)

## የድርሰት ማኅበር ሽልማቱን ሊሰጥ ነው

አዲስ አበባ፡ (ኢ.ዜ.አ.)፤ የኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር ካወዳደረ በኋላ፤ አሸናፊ ለሆኑ አምስት ሰዎች ሽልማት እንደሚሰጥ ተገለጠ፡፡ ማኅበሩ ከልዩ ልዩ ደራሲያን የቀረቡለትን ፺፩ የግጥም ድርሰቶች በታወቁ የሥነጽሑፍ ሰዎች ዳኝነት አስመርምሮ ፹፱ የሚሆኑት የውድድሩ ተካፋይ ከሆኑ በኋላ፤ ለመጨረሻ ውጤት አምስት የድርሰት ባለቤቶች አሸናፊዎች በመሆናቸው የተዘጋጀውን ሽልማት እንደሚያገኙ የድርሰት ማኅበር የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አስታወቀ፡፡

የማኅበሩ ምክትል ሊቀመንበሩ አቶ አበራ ጀምበሬ እንደገለጡት፤ የድርሰቱ ውድድር ውጤት በተስተካከለ ዳኝነትና በምሥጢር የተጠበቀ ከመሆኑም በላይ፤ በጥንቃቄ የተመረመረ በመሆኑ ሽልማቱ በመጀመሪያ ደረጃ የተመሠረተ ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር የአሁኑን ሽልማት የሚሰጠው ወደፊት የተሻለ ድርሰት ለማግኘት፤ ደራሲያንን ለማነቃቃትና የሥነጽሑፍን ቅርስና የቅኔን ውበት ለተከታዩ ትውልድ ለማቆየት ሲሆን ማኅበሩ ወደፊት የተሻሉ ጽሑፎችን በመጠበቅ ላይ መሆኑን ምክትል ሊቀመንበሩ በተጨማሪ ገልጠዋል፡፡

(ሐምሌ 10 ቀን 1960 ከወጣው አዲስ ዘመን)

## በጉርሱም አውራጃ የዝኆን መንጋ ጉዳት ማድረሱ ተገለጠ

ጅጅጋ፤ (ኢ.ዜ.አ.)፤ በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት የጅጅጋና የጉርሱም አውራጃ ግዛቶችን በሚያዋስነው ሰሰም ገብድሌይ በተባለው ቀበሌ የዝኆን መንጋ ጉዳት ማድረሱ ተገለጠ፡፡

ኰሎኔል ይልማ ተሾመ የአሥረኛ ብርጌድ ዋና አዛዥና የሰሜን ክፍለ ግዛት የበላይ አስተዳዳሪ ፊታውራሪ በሽር ሼክ አብዲ የጅጅጋ አውራጃ ገዢ እና ኰሎኔል ማሞ አስፋው የሰሜን ክፍለ ግዛት ፖሊስ ዋና አዛዥ ትናንት ወደዚሁ ሥፍራ ሔደው ሁኔታውን ተመልክተዋል፡፡

ባለሥልጣኖቹ እንደገመቱት የዝኆኑ መንጋ በአካባቢው ሕዝብ አዝመራ ላይ ያደረሰው ጉዳት ጉልቶ ባይታይም፤ ለወደፊት በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ባለው ሰብል ላይ ሕዝቡ ተገቢውን የሆነ ጥበቃ ካላደረገ ጉዳት እንደሚያደርስ ገምተዋል፡፡

እንዲሁም ባለሥልጣኖቹ በጅጅጋ አውራጃ ግዛት በተለይ የዝኆኑ መንጋ ወደሚገኝበት ወደ ጉላ አጆ ተጉዘው በዚያም የዝኆኑ መንጋ በሰብል ላይ ያደረሰውን ጉዳት በመመልከት ለወደፊት መፍትሔ በሚሆኑ ጉዳዮች ላይ ተነጋግረዋል፡፡

(ነሐሴ 11 ቀን 1960 ከወጣው አዲስ ዘመን)

# ዓለም አቀፍ



## የኬንያ ፍ/ቤት የዊሊያም ሩቶ አሸናፊነትን አፀና ራይላ ኦዲንጋ በምርጫ ያሳቸውን ቅሬታ ወደ ኬንያ ፍርድ ቤት አቅርበው ነበር

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የኬንያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኬንያ በተካሄደው ፕሬዚደንታዊ ምርጫ የዊሊያም ሩቶ አሸናፊነትን አፀና።

በኬንያ የተካሄደውን ምርጫ ተከትሎ በፕሬዚደንታዊ ምርጫው ለ5ኛ ጊዜ በዕጩነት የቀረቡት ራይላ ኦዲንጋ የምርጫውን ውጤት አልቀበልም በማለት ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ወስደው ነበር።

የአገሪቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትላንትናው እለት ጉዳዩ ላይ ብይን የሰጠ ሲሆን፤ በዚህም የራይላ ኦዲንጋን ክስ ውድቅ ማድረጉን አስታውቋል።

ፍርድ ቤቱ ቀደም ብሎ በአገሪቱ የምርጫ ኮሚሽን አሸናፊ የተባሉት ዊሊያም ሩቶ የአገሪቱ ተመራጭ ፕሬዚደንት መሆናቸውን የሚያሳየውን ውጤት አጽንቷል።

ይህንን ተከትሎም ተመራጩ ፕሬዚደንት ዊሊያም ሩቶ የፊታችን መስከረም 3 ቃለ መሃላ እንደሚፈፅሙ ሲ.ጂ.ቲ.ኤን ዘግቧል።

ኬንያዊያን ባገባደድነው ነሃሴ ወር ላይ ፕሬዚደንታቸውን ለመምረጥ ድምጽ ሰጥተው ነበር። ይህንን ተከትሎም በአገሪቱ የምርጫ ኮሚሽን ዊሊያም ሳሞይ ሩቶ 50 ነጥብ 49 የሚሆነውን የመራጮች ምርጫ ድምጽ በማግኘት ማሸነፋቸው መገለጹ ይታወሳል።

ሆኖም ግን የ 77 ዓመቱ ራይላ ኦዲንጋ በአገሪቱ የተካሄደው ፕሬዚደንታዊ ምርጫ ውጤት ተቀባይት እንደሌለው በመግለጽና "አልተሸነፍኩም" በሚል የፍርድ ቤት ደጃፍ ላይ ደርሰዋል።

ኦዲንጋ በመከራከሪያነት ያነሱት፤ አራት የምርጫ ኮሚሽን አባላት የምርጫ ውጤቱን አናጸድቅም ብለዋል ማለታቸው እና የውጤቱ ድምር 100 ነጥብ 01 መምጣቱን ነው።

የኬንያ ፍርድ ቤት ከኦዲንጋ የቀረበለትን ቅሬታ በመመልከት ነው የዊሊያም ሩቶን አሸናፊነት ያፀናው።

ዊሊያም ሩቶ ተቀናቃኛቸውን ራይላ ኦዲንጋን በ50.49 በመቶ በሆነ ድምፅ ማሸነፋቸውን የምርጫ ኮሚሽኑ ይፋ መደረጉ ይታወሳል፡፡

ዊሊያም ሩቶ የኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢን በምርጫ ቀደም ብለው ማሸነፋቸውን የአገሪቱ የምርጫ ኮሚሽን አስታውቋል።

ዊሊያም ሩቶ ተቀናቀኛቸውን ራይላ ኦዲንጋን በጠባብ ውጤት ሲመሩም ቆይተዋል። በምርጫው 22 ሚሊዮን ኬንያውያን ተመዝግበው ነበር።

በኬንያ ፕሬዚደንታዊ ምርጫ ለ5ኛ ጊዜ በዕጩነት የቀረቡት ራይላ ኦዲንጋ ይፋ የተደረገውን የምርጫ ውጤት አልቀበልም በማለት ወደ ፍርድ ቤት ማቅናታቸው ይታወሳል፡፡

**የመረጃ ምንጭ**፡- አል -ዐይንና ሲ.ጂ.ቲ.ኤን ናቸው፡፡



## በሱዳን በጎርፍ የተወሰዱ ሰዎች ቁጥር 112 ደረሰ

- በጎርፉ ከ83 ሺህ በላይ መኖሪያ ቤቶች ሲወድሙ 250 ሺህ ሰዎች ደግሞ ተፈናቅለዋል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በሱዳን በጎርፍ የተወሰዱ ሰዎች 112 ደርሷል። በመስከረም ወር ተጨማሪ ዜጎች ለጎርፍ አደጋ ሊጋለጡ እንደሚችሉ ተገልጿል፡፡

በሱዳን ካሳለፍነው ሰኔ ወር ጀምሮ በተከሰተ የጎርፍ አደጋ የሞቱት ሰዎች ቁጥር ወደ 112 ማሻቀቡን ሮይተርስ ዘግቧል፡፡

የዓባይ ወንዝ የውሃ መጠን በመጪዎቹ ቀናት የበለጠ ሊጨምር እንደሚችልም የገለፁት የአገሪቱ የአደጋ መከላከል ባለስልጣናት አስጠንቅቀዋል።

ባለስልጣናቱ በዚህ ወር ብቻ ባጋጠመ አደጋ 112 ሱዳናውያን መሞታቸውንና 115 ሰዎች ደግሞ መጎዳታቸውን አስታውቀዋል። በድምሩ 84 ሺ 40 ቤቶች ሙሉ በሙሉ እና በከፊል መውደማቸው እና መጎዳታቸውንም ተናግረዋል ባለስልጣናቱ።

መሠል የጎርፍ አደጋዎች ለሱዳን አዲስ የተባለ ሲሆን፤ ክረምት በመጣ ቁጥርም እንደሚያጋጥም ተገልጿል፡፡ ሆኖም ዘንድሮ በ1940ዎቹ ካጋጠመውና የከፋ ነበር ከተባለለት የበለጠ የጎርፍ አደጋ ማጋጠሙ ነው የተነገረው።

አደጋው ካለፉት ሁለት የክረምት ወራት ይልቅ በነሐሴ እና መስከረም ወራት ይከፋል መባሉም ብዙዎችን አስግቷል።

የጎርፍ አደጋው በስድስት ግዛቶች እየከፋ የመጣ ሲሆን፤ የአገሪቱ ወታደራዊ መንግስትም በእነዚህ ግዛቶች የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጇል።

በጎርፍ አደጋው ናይል፣ ዋይት ናይል፣ ኮርዶፋን፣ ዳርፉር እና ካሳላ ግዛቶች በጎርፍ አደጋው ክፉኛ ተጎድተዋል ተብሏል፡፡

እስካሁን ባለው የጎርፍ አደጋ ከ250 ሺህ በላይ ዜጎች ከመኖሪያ ቤታቸው የተፈናቀሉ ሲሆን በቀጣዮቹ ሳምንታት ተጨማሪ ጉዳት ሊከሰት እንደሚችል ተጠቅሷል።

በተደጋጋሚ በተከሰተው የጎርፍ አደጋ ሰለባዎችም መኖሪያቸውን አጥተው በጊዜያዊነት በድንኳን ውስጥ ለመጠለል እና እርዳታ ለመጠባበቅ ተገደዋል።

የምረጃው ምንጭ፡- ቢቢሲና ሮይተርስ ናቸው፡፡

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# ማክሰኞ ስፖርት

አዲስ ዘመን

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የኢትዮጵያ እግር ኳስ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ቀንዲሎች

**ቦጋለ አበበ**

ስፖርትን በተለይም እግር ኳስን በዘመናችን ከውድድርነት ባለፈ አርቆ አለመመልከት አላዋቂነት ነው፡፡ ይህ የዓለማችን ቁጥር አንድ ተወዳጅ ስፖርት እግር ኳስ ተሰባስቦ ቂሪላ ከማልፋት በእጅጉ የተሻገረ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፋይዳው እየጎላ ስለመምጣቱ የማይረዳ አለ ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ዘወትር የትችት ናዳ በሚወርድበት የኢትዮጵያ እግር ኳስ እንኳን ስፖርቱ ከሚፈስበት ረብጣ ገንዘብ አንፃር ውጤቱ አገርን ባይመጥንም ፋይዳው በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ እግር ኳስ ሕዝብ የሚመጥነውን ውጤት ባለማግኘቱ ምክንያት የስፖርቱ ማህበራዊ ፋይዳ ብዙ ጊዜ ጎልቶ ሲነገር አይታይም፡፡ የዛሬው እለት የበጎ ፍቃድ ቀን ነውና በዚህ አጋጣሚ መመስገን ያለባቸው ሁለት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ቀንዲሎች የበጎ ፍቃድ ተግባራትና እንቅስቃሴ መነሳቱ የግድ ነው፡፡ ይህም በስፖርቱ እንቅስቃሴ ውስጥ ለሚገኙ ለሌሎች አርአያ ከመሆኑ ባሻገር እንደ አገርም በሌሎች ዘርፎች ትኩረት እንዲሰጠው ያስችላል፡፡

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ስፖርትና የበጎ ፍቃድ እንቅስቃሴ ጉዳይ ሲነሳ የስፖርት ቤተሰቡ በተመሳሳይ ድምፅ የሚመሰክረው አንድ ነገር አለ፡፡ ይህም የቅዱስ ጊዮርጊስና ኢትዮጵያ ቡና ክለብ ደጋፊዎች ናቸው፡፡ የሁለቱ ክለብ ደጋፊዎች በተናጠል በመሰረቱት ማህበርም ይሁን ከማህበራቸው እንቅስቃሴ ውጪ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶችን




**የቅዱስ ጊዮርጊስና ኢትዮጵያ ቡና ክለቦች እንዲሁም ደጋፊዎች በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ለሌሎች ምሳሌ ናቸው፣**

ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በመስጠት ረገድ ከእነሱ ልቆ ሊጠቀስ የሚችል የስፖርት ቤተሰብ የለም፡፡

ቅዱስ ጊዮርጊስና ኢትዮጵያ ቡና እንደ ክለብ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ዋልታና ማገር ሆነው ማገልገላቸውና እያገለገሉ እንደሚገኙም ይታወቃል። ሁለቱ ክለቦች እንደ ተቋም የተለያዩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶችን ለማህበረሰቡ ያበረክታሉ፡፡ ከዚያ በዘለለ ግን የሁለቱ ክለብ ደጋፊዎች በማህበራቸው በኩል የሚያደርጉት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በገንዘብ የማይተመን ለሌሎችም ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ነው፡፡ የደጋፊ ማህበራቱ በስራቸው በሚገኙ በርካታ ውብ ደጋፊዎች አማካኝነት ባለፉት በርካታ ዓመታት የስራቸውን ያህል አልተነገረላቸውም እንጂ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ያላደረጉት ነገር የለም፡፡

የአንጋፋው ክለብ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደጋፊዎች በታላቁ የክለባቸው አርማና የኢትዮጵያ ስፖርት አባት ‹‹ዝክረ ይድነቃቸው ተሰማ›› በሚል በየዓመቱ የደም ልገሳ መርሃግብር ያደርጋሉ፡፡ ሰኔ 17/2010 ዓ.ም ላይ በ9ኛ ዙር የደም ልገሳ መርሀ ግብራቸው በአንድ ቀን 1025 ዩኒት ደም በማሰባሰብ ግንባር ቀደም የሆኑበት ታሪክ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚረሳ አይደለም፡፡ ይህ የበጎ ፍቃድ ተግባራቸው በየዓመቱም ቀጥላል፡፡ የኢትዮጵያ ቡና ደጋፊዎችም በዚህ ረገድ የተለየ ታሪክ የላቸውም፡፡ ቡናማዎቹ በተለይም በየአመቱ በሚያካሂዱት የጎዳና ላይ የቤተሰብ የሩጫ ውድድር ላይ የደም ልገሳ መርሃግብርን ጨምሮ በተለያዩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶችን ለማበርከት ሁሌም ከፊት ተሰላፊ ናቸው፡፡

የሁለቱ ክለብ ደጋፊዎች በተለይም የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተከስቶ የዓለም ስጋት በነበረበት በዚያ በጨለማ ዘመን በተለያዩ በጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ከማህበረሰቡ ዘንድ የቆሙበት አጋጣሚ ታሪክ የሚዘነጋው አይደለም፡፡ በርካታ ገንዘብ በማዋጣት የሕክምና መገልገያ ቁሳቁሶችን ገዝተው ድጋፍ ከማድረግ ጀምሮ በየጎዳናው እጅ እያስታጠቡ ማህበረሰቡ ከወረርሽኙ ራሱን እንዲከላከል ተግተው ሰርተዋል፡፡ ግንዛቤ ከማስጨበጥ ስራዎች ጎን ለጎን ገንዘብ እያሰባሰቡ በወረርሽኙ ሳቢያ ድሃው ማህበረሰብ ለችግር እንዳይጋለጥ ጥረዋል፡፡ በዚህም የብዙዎችን ቀዳዳ ደፍነዋል፣ ለበርካቶችም የእለት ጉርስ ሆነዋል፡፡

ሁለቱ የኢትዮጵያ ሃያላን ክለቦች በሜዳ ላይ ተቀናቃኝ ሆነው ቢታዩም ውብ ደጋፊዎቻቸው በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ብዙ የሚያመሳስላቸው ጉዳይ አለ። ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች በተጨማሪ የአረጋውያንና አእምሮ ሕሙማን የረድኤት ተቋማትን በተለያየ ጊዜ መደገፍ መለያቸው ነው። አቅም ለሌላቸው ተማሪዎች የትምህርት መሳሪያ ቁሳቁስ በማሰባሰብ ድጋፍ ከማድረግ ጀምሮ በችግኝ ተከላና ሌሎች የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶችን ለአገር አበርክተዋል። መቀመጫቸው ከሆነችው አዲስ አበባ ውጪም በተለያዩ ከተሞችና ገጠር ጭምር ዘልቀው የእንቦጭ አረምን ነቅለዋል፣ አንበጣን ለመከላከል ከገበሬው ጋር ሰብል ሰብስበዋል፡፡

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ከሁለቱ ታላላቅ ክለቦች ባሻገር በርካታ የከተማ ክለቦች በተለያየ ደረጃ በሚካሄዱ ውድድሮች ተሳታፊ ናቸው። ይሁን እንጂ ብዙዎቹ ክለቦች ጠንካራ የደጋፊ ማህበር በማቋቋም ረገድ ካለባቸው ክፍተት ጋር ተያይዞ ሊሆን ይችላል ደጋፊዎቻቸው እምብዛም የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶችን ሲያከናውኑ አይስተዋልም። በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚገኙ የበርካታ ክለቦች ደጋፊዎች እንደ ኢትዮጵያ ቡናና ቅዱስ ጊዮርጊስ ደጋፊዎች ሁሉ በበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ብዙ ነገሮችን የመለወጥ አቅም አላቸው። በየአካባቢያቸው በተለያየ መልኩ የተቸገሩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ህይወት መቀየር ይችላሉ። ጥቂት ቢሆኑም በርካታ ደጋፊዎች ያሏቸው አንዳንድ ክለቦች ወጥ ሆኖ ባይዘልቅም ጥሩ ጅምር አላቸው። የሚያስተባብር ጠንካራ የደጋፊ ማህበር የመፍጠር አቅም ላይ ሲደርሱም ተጨባጭ ለውጥ እንደሚያመጡና የእግር ኳስን ትርጉም ከፍ እንደሚያደርጉም ይታመናል። ለዚህ ግን ከሁለቱ የበጎ አድራጎት ተምሳሌቶች ቅዱስ ጊዮርጊስና ኢትዮጵያ ቡና ደጋፊዎች ብዙ መማር ይጠበቅባቸዋል።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)

ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

# አወንታዊ ማኅበራዊ ካፒታል ለኅብረት ሥራ ማኅበራት ውጤታማነት

**በዳንኤል አበበ**

አዳም ስሚዝ የተባለው እውቁ የምጣኔ ሀብት ተጠባቢ በነፃ የገበያ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ እና ዕድገት ውስጥ ገበያውን እንደሻቸው የሚዘውሩ እጃቸው የማይታይ ኃይሎች አሉ እንደሚለው ሁሉ የአንድን አገር የኢኮኖሚ ልማት እና የሠላም አቅጣጫ የሚወስኑ ማኅበራዊ ካፒታሎች (Social Capitals) አሉ። ማህበራዊ ካፒታል የማይዳሰስ ሀብት ነው።

በዓለማችን የተለያዩ የካፒታል አይነቶች አሉ። የተፈጥሮ፣ የፖለቲካ፣ የንዋይ (የፋይናንስ) እና የሰው ሃብት። ከሁለት እና ሶስት አስርት ዓመታት ወዲህ የማኅበራዊ ካፒታል ተጨማሪ ሀብት ሆኖ ለኢኮኖሚ ልማትና ለሠላም መረጋገጥ ወሳኝ ምሰሶ ሆኖ ብቅ ብሏል። የማህበራዊ ካፒታል ጽንሰ ሃሳብ በትብብር፣ በተሠናሰነ ግንኙነት፣ በቅርርብ እና በመተማመን የሚገነባ እና የሚገራ ጽንሰ ሃሳብ እንደሆነ በመገለጫዎቹ ደረጃ ብዙዎች ቢስማሙም፣ ሁላችንን የሚያስማማ ወጥነት ያለው የማኅበራዊ ካፒታል ትርጓሜ የለም።

በማኅበራዊ ሳይንስ አጥኚዎች፣ በፖለቲካ ሳይንቲስቶች እና በምጣኔ ሃብት ጠበብቶች ዘንድ የማኅበራዊ ካፒታል ምንነት ላይ ጠንከር ያሉ ክርክሮች እንደቀጠሉ ናቸው። እውን ማህበራዊ ካፒታል “ካፒታል” ነውን የሚል ጥያቄም የሚያነሱ እና ጽንሰ ሃሳቡን የሚሞግቱ ምሁራን ቁጥራቸው የሚናቅ አይደለም። በምንነቱ አረዳድ እና በብያኔ አሰጣጥ ላይ ወጥነት ያለው ስምምነት ባይኖርም ምሁራኑ በአንድ መሠረታዊ ነጥብ ይስማማሉ። ይህውን ፊልድ የሚባል የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪ ማህበራዊ ካፒታል ማጠንጠኛው የሰዎች ግንኙነት ነው በሚለው ሃሳብ ።

የማህበራዊ ካፒታል ጽንሠ-ሃሳብ ውስብስብ እና ለመመዘን የሚያስቸግር ጽንሠ ሃሳብ ነው። ኮልማን የተባለ የማኅበራዊ ሳይንስ አጥኚ ማህበራዊ ካፒታል የግለሠብ ንብረት አይደለም። የካፒታሉ መኖርም ብሎም የካፒታሉ አወንታዊ ሆነ አሉታዊ ውጤቶች እና አንድምታ እንዳለው የሚታወቀው ሰዎች በአኗኗራቸው ሲተገብሩት ወይም ሠዎች በማኅበራዊ ግንኙነታቸው ውስጥ ሲጠቀሙበት ነው ይላል።

በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ በዋንኛነት ሁለት ዓይነት ማኅበራዊ ካፒታሎች እንዳሉ የማኅበራዊ ካፒታል አጥኚዎች ይናገራሉ። አንደኛው አወንታዊ ማኅበራዊ ካፒታል) ሲሆን፣ ሁለተኛው አሉታዊ ማኅበራዊ ካፒታል ይባላል። አወንታዊ ማኅበራዊ ካፒታል የሚባሉት ከህብረተሰቡ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ ሃይማኖት ውስጥ የሚመነጩ ለሰው ልጆች ለሁለንተናዊና አወንታዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ያላቸው ሃብቶች ናቸው። አሉታዊ ማህበራዊ ካፒታል የሚባሉት ደግሞ በግለሠቦች፣ በማህበረሰብ ብሎም በቡድኖች መካከል የመጠራጠር፣ የመራራቅ፣ የመከፋፈል እና በጠላትነት የመተያት አዝማሚያዎች እና ነፀብራቆች ባብዛኛው የሚስተዋልበት እና በቀጣይ ምን ሊከሰት ይችላል ተብሎ ለመተንበይ አዳጋች የሚሆንበት ሁኔታዎችን የሚያካትት ሲሆን፣ ከዛም አለፍ ሲል ግጭቶች እንዲፈጠሩና በዚህም ሳቢያ አገርን የማፍረስ እና የመበተን አቅም ያለው የማይዳሰስ አሉታዊ ካፒታል ነው።

ለአብነት ያህል የአወንታዊ ማኅበራዊ ካፒታል ምንነትን ለማስረዳት በአገራችን የዕቁብ ወይም የእድር ተቋማት ‘ገቨርናንስ’ ጠጋ ብሎ መቃኘት ይበቃል። የተለያዩ ኃይማኖት፣ ጎሳ፣ ዘር፣ የፖለቲካ አመለካካት እና አቋም ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚሠበሰቡበት ተቋም ነው። ተቋማቱ በግለሠብ ማኅበረሰብ አባላት ላይ ለሚደርሱ ማህበራዊ ችግሮች ግንባር ቀደም ደራሾች ከመሆናቸው ባሻገር የተለያዩ የማህበረሰብ አባላትን በሠላምና በትብብር መንፈስ ተቻችለው እንዲኖሩ ያቀራርባሉ፣ ቅሬታም፣ አቤቱታም ሲፈጠር የመደማመጥ፣ የመመካከር፣ የመከባበር፣ የመተዛዘን ዕድል ይፈጥርላቸዋል። በዚህም በመካከላቸው መተማመን ይዳብራል፣ እሴቶችና ልማዳዊና ማህበረሰባዊ ህጎች ይዳብራሉ።

ዴስ ዳቮስ የተባለ የምጣኔ ሃብት ምሁር የኅብረት ሥራ ማኅበራት መርሆች ከማኅበራዊ ካፒታል ጽንሠ ሃሳቦች ጋር የተሳሰሩ ናቸው። የጋራ ጥቅምን ማዕከል ያደረገ ውሳኔ፣ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ተሳትፎ፣ የጋራ ሃብትን ለጋራ ተጠቃሚነት ምቹ ማድረግ የሚሉ መሠረታውያን (Elements) በኅብረት ሥራ ዘርፍ መርሆችም ሆነ በማህበራዊ ካፒታል ጽንሠ-ሃሳቦች ውስጥ የተካተቱ የመሰረት ድንጋዮች ናቸው ይላል።

የኅብረት ስራ የማዕዘን ድንጋዮች የሚባሉት ከሰባቱ የዘርፉ መርሆች መካከል ሁለቱን መርሆች ማለትም “በኅብረት ሥራ ማኅበራት መካከል ትብብር” እና የአባላት በምጣኔ ሀብት ተሳታፊነት ብቻ ወስደን ከማህበራዊ ካፒታል መገለጫዎች ከሆኑት መተማመንን፣ የኅብረተሰብ ኔትወርክን (ማኅበራዊ ቅርበቶች፣ መተሳሰቦች እና መተባበር)፣ ለጋራ ጥቅም በጋራ ለመስራት መስማማት፣ መደጋገፍ (Reciprocity)፣ ልምዶች (Norms) ወይም በማኅበረቡ ውስጥ ተቀባይ ያላቸው እና የሌላቸው ተግባራትና አስተሳሰቦች ስንመለከት የኅብረት ሥራ ዘርፍ መርሆች እና የማህበራዊ ካፒታል መገለጫ ባህሪያት ይጣጣማሉ ለማለት ያስችለናል።

በአገራችን ኢትዮጵያ በኅብረት ሥራ ማህበራት ‘ገቨርናንስ’ ውስጥ ማህበራዊ ካፒታል በኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት ተሳትፎ እና የሥራ አፈጻጸም ላይ ስለሚያመጣው አወንታዊ ፋይዳ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ተግባራዊ ጥናቶች ተደርገው አያውቁም።

ማህበራዊ ካፒታል ምጣኔ ሃብትን እና ሠላምን በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ እንዲጠናከር ለማድረግ መንግስት ማህበረሰብ-ተኮር ማህበራዊ ካፒታልን የሚያሳድግ ፖሊሲዎች ሊያወጣ ይገባል። በኅብረት ሥራ ማኅበራት አደረጃጀት ውስጥ አወንታዊ ማህበራዊ ካፒታልን እንደ ማበልፀጊያ ማዕከላት የመጠቀም እምቅ ዕድሉ አለ።

በብዙ ዓመታት የተገነቡ ሚዛናቸውን ጠብቀው የሚያድጉ ማኅበራዊ ድሮች (ማኅበራዊ ካፒታል) የሰዎች መተዋወቅ፣ መከባበር፣ መተሳሰብ ዋጋው ከሌሎች ሃብቶች በላይ በመሆኑ እንደ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ያሉ ተቋማት አለመግባባትን፣ ግጭትን ለመፍታት እና ዘላቂ ሠላም እንዲመጣ ከመደበኛው አደረጃጀቶች የተሻሉ በመሆናቸው አወንታዊ ማህበራዊ ካፒታል በዕቅድ ታስቦባቸው ሊገነቡ ይገባል።

በርካታ የፖለቲካል ኢኮኖሚ እና ኢኮኖሚክ ሶሲዮሎጂስት ጥናቶች እንደሚያሳዩት ማህበራዊ ካፒታል ለምጣኔ ሃብት እና ለማህበራዊ ልማት ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ማኅበራዊ ካፒታል ፖሊሲን አይተካም። ይሁን እንጂ ለልማት ፖሊሲዎች እንዲሁም ለሌሎች ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ አካባቢያዊ እና ቴክኖሎጂካል ፖሊሲዎች ቀረጻ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያለው እና ገዢ የሆነው ማኅበራዊ ካፒታል ግምት ውስጥ ሊገባ እና ሊፈተሽ ይገባል።

በኅብረት ስራ ማኅበራት ውስጥ ያለው ግንኙነት ጤንነቱን ጠብቆ እንዲዳብር፣ በአባላት መካከል ያለው ግንኙነት እየላላ ብሎም መተማመን እየከሰመ መጥቶ፣ ትብብር፣ ተግባቦት እና የመተሳሰብ ማህበራዊ ድሮች እንዳያሽቆለቁል በኅብረት ሥራ ማኅበራት ውስጥ ያሉ አወንታዊ ማህበራዊ ካፒታሎች እንዲዳብሩ ሁላችንም ትኩረት ሰጥተን በዕቅድ ልንመራው ይገባል።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et